From the Library of
ፍሥሐ ኣጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

የአማርኛ፡ መጽሔተ-ቃላት።


መስፍን ልሳኑ ።

ባለ አንድና ባለ ኹለት ፊደላት ።
መጀመሪያ ክፍል ።

ተጎትመ ዝንቱ መጽሐፍ በጅወይቱ ዓመተ መንግሥቱ
ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

አዲስ አበባ ፲፱፻፺፪ ዓ . ም .

በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ታተመ ። ቍ 8632



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

« ------ የሀገራችንን ትምህርት በአማርኛና በግዕዝ መማር ትልቅ ጥቅም ያለበት ነው ----------

--------- የሀገራችንን ትምህርት ሳንማር የውጭ ሀገር ትምህርት እማራለኹ ማለት በድቡሽት ላይ ቤት እንደ ሠራው ሰው ምሳሌ ለመኾን ነው ።»

ቀ . ኃ . ሥ .

«ልጅነት የያዘው ምላሳችን መንካ
ከቋንቋችን በፊት ሌላ ቋንቋ አይንካ

ግዕዝ ካማርኛ አስተባብሮ ሲያውቅ
ከውጭ ሀገር ቋንቋ ያን ጊዜ ይንጠቅ ።»

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ።

ሦስተኛው ጐዳና ።

ይኽ ጐዳና ከመጀመሪያው ጋራ ይተባበራል፤ ነገር ግን ግዕዛኑን በመላ አስቀድሞ ሌሎቹንም እንደየግዕርጋቸው እያከታተለ በደኅና አኳኋን ከተጓደደ በኋላ ከቃላት ብዛት ማጠር የተነሣ አካኼዱ ስለሚሳከር ካገልግሎት ታግዶአል ።

ሀ	ለየ	ለመነ	ለመለመ	ተመለከተ
ለ	አሸ	ለመደ	ለመዘገ	ተመረኰዘ
ሐ	አዠ	ለመጠ	ለመጠጠ	አመሰገነ

በተገለጸው ማስረጃ መሠረት በመልካም አኳኋን መከናወን ከጀመረ በኋላ ባለ ሥድስት ፊደላትና ከዚያም በላይ ወደ ኾኑት ቃላት ሲደርስ መሳከሩን ተመራማሪ ጐዳናውን ተጠቀሞአልና ቢፈልግ ይድረስበት ።

አራተኛው ጐዳና ።

ይኽ ጐዳና አያሌውን ጊዜያት የአውሮጳውያን መጽሔታተ - ቃላት የሚዘጋጁበት ነው ። የፊደላትን ተራ ብቻ የሚጠብቅ ሲኾን ያማርኛን ቃላት በእርግጠኛ ባሕርያዊ ሥነ ጽሑፋቸውና አነባበባቸው ለመወሰን የማይችል በመኾኑ ላማርኛችን ጠቃሚ ስላልኾነ አገልግሎቱን ፈላጊዎች ከመኾን ታገድን ።

ጐዳናውም መነሻቸው ሀ በኾኑ ቃላት ከዚኽ በታች ተገልጾአል ።

ሀገር	ሁከት	?	ሃሌ	?	ህላዌ	ሆሣዕና
ሀሁ	ሁዳዴ	?	ሃይ	?		ሆይ
ሀብት	ሁዳድ	?	ሃይማኖት	?		ሆድ

ምሳሌ ፤ ማርና ወተት ምን አገናኝቶት ባይ ከኾነ ፤ ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ እንደ ሚባለው ጐሉ ያማርኛ መጽሔተ - ቃላት የቃላትን ባሕርያዊ ሥነ ጽሑፋቸውን አነባ በባቸውንና ተራቸውንም በጠነቀቁ ፤ በተመለከቱ በሦስት ዐይነት ታላላቅ ጐዳናዎች ሊዘጋጅ ሲችል ፤ ማርን አምርሮ ወተትን አጥቅሮ ፤ ይኽን አማርኛችንን መወሰን የማይችል አራተኛውን ጐዳና መምረጥ በቋንቋችን ላይ ከሚጥለው እንከን ይልቅ ተፈጥሮን ካለማወቅ አያስቈጥርምን ? ።

አ ።

የአ ፊደል እንዳይዋጥ ምንም እንኳ ከዚኽ በፊት የታሰበበት ቢኾን ጊዜያትን በሚያመለክቱ አናቅጽ መድረሻ ላይ ካልኾነ በስተቀር ይኽ አስተያየት እንዲጸና ማድ ረግ አጥጋቢ አይደለም ፤ እንዲረጋ ከተፈለገ ግን ያማርኛ አጻጻፍ ይለወጥ ከማለት ያደ ርሳል ። ይኽንኑም ከዚኽ በታች በተገለጸው ማስረጃ መመልከት ነው ።

የቀለጠፈው ።		መሠረት ።
ባላምበራስ	=	በአለአምባራስ
እያከታተለ	=	እየአከተአተለ
ማባበል	=	መአበአበል

ከዚኽም በላይ ጥንት በግዕዛን ፊደላት ብቻ ይነገር እንደ ነበረ ወደ ማስተዋል ያዘነበልን እንደ ኾነ ከሚቀጥለው አስተያየት እንደርሳለን ።

የቀለጠፈው ።		መነሻው ።
መስፍን	=መሰእፈእነእ=	(መ) ሰፈነ

ማስገንዘቢያ ።

ሰባቱን ግዕርጋተ - ፊደላት በመጠበቅ ፤ የፊደላትን ተራ በመጠንቀቅ ፤ የቃላትን አነባበብ በማመልከት ፤ ያማርኛን ባሕርያዊ ሥነ ጽሑፍ በማጽናት ላይ ያለውን ሐተታ ፡ የእንስሳት ፤ የአራዊት ፤ የዕፀዋት ፤ የአዕዋፍ የቁሳቍስ ፤ እነዚኽንም የመሳሰሉት ፤ በጠቅላላ ፍጥረታቸው ለሥዕል የሚመቹትን ጉሉ በመግለጽ ፤ ከውጭ አህጉር የተወ ረሱትን ቃላት በማከል ፤ ተዘጋጅቶ በሚወጣው መጽሔተ - ቃላት ውስጥ እየተነተንን በማስረጃም እያጸደቅን ሥራችንን ለማጽናት ፤ እንዲዘገይ ተደርጎአል ።

መጠቈሚያ ።

(ሀ) ባናታቸው ላይ ይዘት (.) የተደረገባቸው ፊደላት ከቅንጃቸው ጋራ ተናብበው መጥበቃቸውን ይገነዘብዋል ለማ ።

ባናታቸው ላይ ድርብ ሰረዝ (¨) የተደረገባቸው ፊደላት ከቅንጃቸው ጋራ ተናብ በው በፍጥነት አነጋገር መጥበቃቸውን መገንዘብ ነው ። ብስ ።

በኹለት ነጥብ (፡) የተመለከቱት ሳይናበቡ የሚጠብቁ ናቸው ። ጥዝ ።
ያልተመለከቱት ግን እየተናበቡ እንደ ፊደሉ ደንብ የማይጠብቁ ናቸው ።

(ለ)=በዚኽ እኩያነትን ፤ እኩልነትን በሚገልጽ ምልክት የተመለከቱት ጉሉ ፍቻቸው ያው ነው ።

(ሐ) ※ ይኽ ምልክት ፤ ቃሉ ኹለት ፍች እንዳለው ይገልጻል ።

መ ሠ ረ ታ ዊ የ አ ማ ር ኛ ፊ ደ ል ።

አ	ቡ	ጊ	ዳ	ሄ	ው	ዘ
በ	ጉ	ዲ	ሃ	ቄ	ዝ	ሐ
ገ	ዱ	ሂ	ዋ	ዜ	ሕ	ሾ
ደ	ሁ	ዊ	ዛ	ሐ	ሸ	ጠ
ሀ	ዉ	ዚ	ሐ	ሼ	ጥ	ዮ
ወ	ዙ	ሐ	ሻ	ጤ	ይ	ጆ
ዘ	ሑ	ሺ	ጣ	ዬ	ች	ኮ
ሐ	ሹ	ጢ	ያ	ቼ	ክ	ሎ
ሸ	ጡ	ዩ	ጅ	ኬ	ል	ኾ
ጠ	ዩ	ቺ	ካ	ሌ	ኻ	ሞ
የ	ቹ	ኪ	ላ	ኼ	ም	ኖ
ቸ	ኩ	ሊ	ኛ	ሜ	ን	ሦ
ከ	ሉ	ኺ	ማ	ኔ	ሥ	ኽ
ለ	ኹ	ሚ	ና	ሔ	ኽ	ያ
ኘ	መ	ኒ	ሣ	ኼ	ዕ	ፎ
መ	ኑ	ሢ	ኻ	ዔ	ፍ	ዥ
ነ	ሡ	ኺ	ዓ	ፌ	ዥ	ጸ
ሠ	ኽ	ዒ	ፋ	ዤ	ጽ	ቆ
ኽ	ዑ	ፊ	ዣ	ጼ	ቅ	ጆ
ዐ	ፉ	ዢ	ጻ	ቄ	ጅ	ያ
ፈ	ዤ	ጼ	ቃ	ጇ	ዕ	ጮ
ዣ	ጼ	ቂ	ጃ	ቂ	ጭ	ኖ
ጸ	ቁ	ጇ	ዓ	ጩ	ጎ	ሶ
ቀ	ጁ	ዊ	ጫ	ጒ	ስ	ፅ
ጀ	ፀ	ፍኒ	ኃ	ሴ	ጵ	ሮ
ፀ	ፍኩ	ኒ	ሳ	ጁ	ር	ቶ
ፍኩ	ጎ	ሲ	ፅ	ሬ	ት	ፖ
ጎ	ሱ	ጁ	ራ	ቱ	ፕ	አ
ሰ	ጼ	ሪ	ታ	ፔ	እ	በ
ጸ	ሩ	ቲ	ፓ	ኤ	ብ	ጎ
ረ	ቱ	ፒ	አ	ቤ	ግ	ዶ
ተ	ፑ	ኢ	ባ	ጌ	ድ	ሆ
ፕ	ኡ	ቢ	ጋ	ይ	ህ	ዎ

ሕ ፀ ፃ ነ ማ ዕ ር ግ ።

ጐ	ኩ	ቋ	ኌ	ጕ
ኩ	ቍ	ኋ	ጌ	ኵ
ቈ	ጕ	ጓ	ኳ	ቍ
ጎ	ጕ	ኳ	ቋ	ጕ

ማ ስ ገ ን ዘ ቢ ያ

ደጅ ጠኝዎች

ኧ	?	?	?	?	?	?
ቨ	ቩ	ቪ	ቫ	ቬ	ቭ	ቮ

፪/ ዲቃሎች

ቾ	ቿ	ቺ	ቻ	ቼ	ችኦ	ኦ
ገሯ	ገሡ	ገሢ	ገሣ	ገሤ	ጎሯ	ገሯ
ጇ	ጁ	ጂ	ጃ	ጄ	ጅ	ጇ
ጨ	ጩ	ጪ	ጫ	ጬ	ጭ	ጮ

፫/ ጎ ጐ ጒ ጋ ጔ ጓ ጖

፬/ ፕ ፤ በኋላ ዘመን የመጣ የአውሮ ጳውያን ፊደል ሲኾን በዘልማድ የጸን ቦታ ለመንጠቅ ይፍጨረ ጨራል ።

ፕ ፑ ፒ ፓ ፔ ፕ ፖ

ማ ሳ ሰ ቢ ያ ።

አማርኛ ከግዕዝ ፤ ግዕዝም ከአብራይስጥና አዓረ ብኛ የተመሠረተ ነው ። ይኸ ሲኾን ከግዕዙ ይልቅ አማርኛ ከዕብራይስጡ ጋራ የቅርብ ዝምድና አለው ። ይኸንኑም እነ ፤ ሸ ፤ ኸ ፤ ባማርኛ ውስጥ ያላቸውን አገልግሎት በመመልከት ይረድዋል ። ይኸ መሠረታዋ ያማርኛ ፊደል ከዕብራይስጡ ፊደል ጋራ በቅደም ተከተል እምብዛም የማይለያይ በመኾኑ ባገልግሎት ውስጥ እንዲውል መስማማት እውነተኛ ሕግን የተ መረኰዘ ጥቅምን አስከታይ ነው ።

አኀዝ ።

	አልቦ	0
፩	አንድ	1
፪	ኹለት	2
፫	ሦስት	3
፬	አራት	4
፭	አምስት	5
፮	ሥድስት	6
፯	ሰባት	7
፰	ስምንት	8
፱	ዘጠኝ	9
፲	ዓሥር	10
፳	ኻያ	20
፴	ሠላሳ	30
፵	አርባ	40
፶	ሓምሳ	50
፷	ሥሳ	60
፸	ሰባ	70
፹	ሰማንያ	80
፺	ዘጠና	90
፻	መቶ	100
፲፻	ሺሕ	1000
፼	እልፍ=ዓሥር ሺሕ	10,000
፲፼	አእላፍ=መቶ ሺሕ	100,000
፻፼	አእላፋት	1,000,000
፲፻፼	ትእልፊት	10,000,000
፼ ፼	ምእልፊት	100,000,000
፲፻ ፼ ፼	አእላፈ-አእላፋት	100,000,000,000
፼ ፼ ፼	አእላፈ-ትእልፊት	1,000,000,000,000
፲፼ ፼ ፼	ትእልፊተ-አእላፋት	10,000,000,000,000
፻፼ ፼ ፼	ምእልፊተ-አእላፋት	100,000,000,000,000
፲፻፼፼፼	ትእልፊተ-ምእልፊት	1,000,000,000,000,000
፼ ፼፼፼	ምእልፊተ-ምእልፊት	10,000,000,000,000,000

በሦስተኛው ዓምድ የተገለጠው አኀዝ በመሠረቱ ዓረብኛ ነው ።

በዛሬው ዘመን ፤ በሒሳብ ረገድ እጅግ በጣም አስፈላጊ በመኾኑ ያገለግለን ዘንድ ከአማርኛው አኀዝ ጋራ እየተነጻጸረ ተጽፎአል ።

ማስገንዘቢያ ። ፼=እልፍ=መቶ ጊዜ መቶ ማለት ነው ።

አማርኛ ግዕዝ

ሀ ሀ ያማርኛ ፊደላት መወጠኛ ።
ሀ ፤ ሳይሉ ጽሕፈት
ውል ሳይዙ ሙግት ።
፪/ የግዕዛን ፊደላት መጀመሪያ ።
ሀ ፤ ባሉ
ደሞዝ በሉ ።
፫/ ሀብት=ሀብት ። ፬/ ስሙ=ሃሌታው ሀ ።
ሀብት ሁከት ውሂብ ሃይማኖት ቡሄ ወሀኒ ሆይ

ለ ለ የሀ ተከታይ ። ፪/ መስተዋድድ ። ለወገኑ ሰጠ ። ለአባቱ ላከ ።
ለቤት ማንቃ
ለሰው አለቃ ።
ለራስ ምታት ጩኸበት
ለሆድ ቍርጠት ብላበት ።
ለሚስት ያጐርስዋል
ለተመታ ይክስዋል ።
፪/ በአናቅጽ አርእስት ላይ እየተጫነ ፤ አድራጊነትን ፤ አስደራጊነትን ፤ ተደራጊነትን ፤ ተደራራጊነትን ፤ አደራራጊነትን ፤ አዳራጊነትን ፤ ተደራጊነትን ፤ ይገልጻል ።
ለመሥራት የሚደፍር
መብላትን አይደፍር ።
ለማስገደል ነው ። ለመግደል ነው ። ለመግዳደል ነው ።
ለማገዳደል ነው ። ለማጋደል ነው ። ለመጋደል ነው ።
፫/ የበጎ ማድረጊያ ። ፈቀደለት ። ፈረደለት ።
፭/ ለብሰ=ለበሰ ።
ለየ ሉድ ሊባ ላላ ሌባ ልጥ ሎጥ ።

ሐ ሐ አ ሦስተኛ ። ፪/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ። ፬/ ሐውልት=ሐውልት
አጌ=ሐጌ ። ፭/ ስሙ=ሐመሩ ሐ ።
ሐውልት እሑድ ሒሳብ ሐሳብ እግዚአብሔር ሕዝብ ብሔር

መ መ አራተኛ ። ፪/ የአናቅጽ አርእስት መነሻ ። መምጣት ፤ መኼድ ።
መለመን የለመደ ምላስ
በሕልሙ አቁማዳን ይዋስ ።
፫/ መስቀል=መስቀል ።
መጣ ሙዳ ሚና ማማ ሚታ ምሳ ሞራ

ሠ ሠ አምስተኛ ። ፪/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ። ሴት ። ሜት ።
፬/ ሠርሐ=ሠራ ። ፭/ስሙ=ንጉሡ ሠ ።

አማርኛ ግዕዝ

ሠራ ንጉሡ መሚሕ ሣለ ሜት ሥራ ሦስት

ረ ረ ሥድስተኛ ። ፪/ረብሐ=ረባ ።
ረባ ሩብ ሪቅ ራራ ሬት ርግብ ሮሮ

ሰ ሰ ዘ ሰባተኛ ። ፪/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ። ሳለ ። ሣለ ።
፫/ ሰማይ=ሰማይ ተዝካር=ተስካር ። ፬/ ስሙ=እሳቱ ሰ ።
ሰባ ሱቲ ሲራክ ሳተ ሴት ስስ ሶራ

ሸ ሠ ሰ ስምንተኛ ። ፪/ መድረሻቸው ሠ ፤ ሰ ለኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ።
ነገሠ—ነጋሽ ፤ መናገሻ ፤ መንገሻ ።
ከሳ—ከሸ ፤ መክሻ ።
፫/ሚመት=ሹመት ። ሲበት=ሽበት ። መስየ=መሸ ።
ሸተ ሹም ሺሕ ሻጣ ጋሼ ቀዳሽ ሙሾ

ቀ ቀ ዘጠነኛ ። ፪/ቀብዐ=ቀባ
ቀባ ቁና ቂጣ ቃታ ቄራ ቅል ቆዳ

በ በ መ ዓሥረኛ ። ፪/ መስተዋድድ ። (ሀ) የማድረጊያ ። በዱላ ቀነደበው ።
(ለ) የቦታ ። በተራራው ላይ አለፈ ፣ (ሐ) የጊዜ ። በሥድስት ሰዓት ይመጣል ።
(መ) አመዛዛኝ ። ባለፈ ነገር አትቈጭ ። ፫/ ያናቅጽ ባዕድ ፣ መነሻ (ለጊዜያት) ። በተሰበረ ። በተሰበረ ነበር ። በመጣ ኖሮ ።
፬/ ስለ ። በእገሌ በሞቱ ። ፭/ በልዐ=በላ ። ዘንመ=ዘነበ ።
በመድሎቱ ልቡ=በልቡ ሚዛን ።
በላ ብቡ ቢያ ባላ ቤት ብዙ ቦይ ።

ተ ተ ዓሥራ አንደኛ ። ፪/የተደራጊና የተደራራጊ የተዳራጊም ፤ መመደቢያ ።
ተገደለ ። ተገዳደለ ። ተጋደለ ። ፫/ ከ ። ተኩል=ከእኩል ።
፬/ ተከለ=ተክለ ።
ተላ ቱር አላቲ ታታ ሰታቱ ትል መቶ ።

ቸ ተ ኀ ፤ ክህ ዓሥራ ኹለተኛ ። ፪/መድረሻቸው ፤ ተ ፤ ለኾኑ ፤ አናቅጽ ፤ ቅጽልን ።
መወሰኛ ። ዛተ—ዛች ፤ መዛቻ ፤ ዛቻ ።
፫/ በልአት=በላች ። ኄር=ቸር ። ክህለ=ቻለ ።
ቸከ ምቹ ቡቺ ቻለ ልቼ ችኮ ቀበርኞ ።

ኀ ኀ ዓሥራ ሦስተኛ ። ፪/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ። ድኅነት ።
ድኽነት ። ፫/ ኀብል=ኀብል ። ፬/ ስሙ=ብዙኃኑ ኀ ።
ኀብል ድኑር ኒሩት ኃይል ርኅራኄ ኀዳር ኖኅት ።

ነ ነ ሐ ዓሥራ አራተኛ ። ፪/ ነገር=ነገር ። ዋሕድ=አንድ ።
ነጋ ኑግ ወህኒ ናዳ ብያኔ ንጉሥ ኖረ

ኘ ነ ዓሥራ አምስተኛ ። ፪/መድረሻቸው ፤ ነ ፤ ለኾኑ ፤ አናቅጽ ቅጽልን
መወሰኛ ። ዳነ—ዳኘ ፤ መዳኛ ። ፫/ አስትየኒ=አጠጣኝ ። ዳን=ዳኛ ።

አማርኛ ግዕዝ

ሸኘ መናኙ መጣ ሸኚ ተኛ ዳኘ ድኝ አኟ

አ አ ሀ፤ሐ፤ኀ፤ ዓሥራ ሥድስተኛ ። ፪/ የአናቅጽ ባዕድ መነሻ (አድራጊነትን የሚገልጽ) ። ፈገፈገ—አፈገፈገ ። መጣ—አመጣ ።

፫/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ። አረፋ ። ዓረፋ ። አርብ ። ዓርብ ።

፬/ ሀለሌ=አለሌ ። ሐለመ=አለመ ። ኀዘለ=አዘለ ። ፭/ ስሙ=አልፋው አ ፤ አለ ኡኡ ኢትዮጵያ አሳብ ኤል እርሱ አሃ

ከ ከ ኀ፤ ዓሥራ ሰባተኛ ። ፪/ መስተዋድድ ። (ሀ) የመነሻ ። ከበረሃ ተመለሰ ። (ለ) የቦታ ። ከቤቱ በላይ ነው ። (ሐ) የጊዜ ። ከሰዓት በላይ ይመጣል ። ፫/ መስተፃምር ። (ሀ) የውልና ። የምክንያት ። ከመጣ ይሰጠዋል ። ከወደደ ዘንድ ይማር ። (ለ) የጊዜ ። ከቁረበች
አፈረሰች ።
ከመነኰሰች
ባሰች ።
(ሐ) አመዛዛኝ ። እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አለች አህያ ።

፬/ ተ
ተወፈሩ
ሰው አይፈሩ ።
ተክፉ ጐረቤት
አይሠሩም ደኅና ቤት ።

፭/ ከፈለ=ከፈለ ። ብኑዕ=ቡኮ ።

ከፋ ኩታ ኪስ ካባ ዘኬ ክር ኮባ

ኸ ኪ ዓሥራ ስምንተኛ ። ፪/ በላእኩ=በላኹ ። ሦክ=እሾኽ ።

፫/ ስሙ=ኹነኛው ኻ ።

ቸኸ ኹለት ኺድ ኻያ ኼደ በላኽ ኾነ

ወ ወ መ፤ ዓሥራ ዘጠነኛ ። ፪/ ወለደ=ወለደ ። መንበር=ወንበር ። መንጠፍት=ወንጠፍት ።

ወዛ ዉሎ ልባዊ ዋልታ ህላዌ ውሻ ቢላዎ

ዐ ዐ ዓያኛ ። ፪/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ። አረፋ ። ዓረፋ ።

፫/ ዓለም=ዓለም ። ዕዉር=ዕዉር ። ፬/ ስሙ=ዓይኑ ዐ ።

ዐበደ ዑደት ዒማ ዓጣ ሱባዔ ሥዉር ተጸውዖ

ዘ ዘ የ፤ ዓያ አንደኛ ። ፪/ ዘርፍ አያያዥ ። ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ = የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ።

፫/ ዘርአ=ዘራ ። ረየመ=ረዘመ ።

ዘባ ዙሃ እግዚአብሔር ዛፍ ዜጋ ዝና ዞማ

አማርኛ ግዕዝ

ዝ ዘ ኻያ ኹለተኛ ። ፪/ዝእብ=ዝብ ።
ዣገር ዙዋ ዝገሮት ጋገር አጋገፎ ዝብ ዣንገር
የ የ ዘ ፤ ኻያ ሦስተኛ ። ፪/ ዘርፍ አያያዝ ። ዘርዬተ ሰላም ነጸፈ=
የፍቅርን ምንጣፍ አነጠፈ ። ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ=
የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ።
የመነሱሴ ሎሌ ።
የክረምት አሞሌ ።
የመስከረም ውስጡ በጋ
ያረመኔ ልቡ ቀጋ ።
፫/ ዮሐንስ=ዮሐንስ ። ረየመ=ረዘመ ።
የት መዩ የዩ ያያ ቀዬ ይኸ ዮሐንስ ።
ደ ደ ኻያ አራተኛ ። ፪/ ደክመ=ደከመ ።
ደማ ዱዳ ዲብ ዳቤ ነጋዴ ድባ ዶግ
ጀ ደ ኻያ አምስተኛ ። ፪/እድ=እጅ ። ዳን=ጃን ።
ባጀ የጁ ቅጂ ጃኖ ወስጂ እጅ ቄንጀ
ገ ገ ኻያ ሥድስተኛ ። ፪/ ገዘረ=ገረዘ=ገዘረ ።
ገባ ጉድ ጊዮርጊስ ጋዳ ጌታ ግራ ጎታ
ጠ ጠ ጸ ፤ ፀ ኻያ ሰባተኛ ። ፪/ጠል=ጠል ። ወጽአ=ወጣ ። ሐፀር=አጥር ።
ጠባ ጡት መናጢ ጣፋ ጤዛ ጥጥ ጠጣ
ጨ ጠ ጸ ፤ ፀ ፤ ቀ ፡ ኻያ ስምንተኛ ። ፪/ጤሰ=ጨሰ=ጤሰ ። ጸልመ=ጨለመ ።
ፄው=ጨው ። ረቀየ=ረጨ ።
ጨሃ ጩቤ አክርማ ቅጪ ጫጫ አገጩ ጭድ ጮቤ
ጰ ጰ ኻያ ዘጠነኛ ። ፪/ ጳራቅሊጦስ=ጰራቅሊጦስ ። ጴጥሮስ=ጴጥሮስ ።
ጰራቅሊጦስ እምጴ ጲላጦስ ጳውሎስ ጴጥሮስ ጵጵስና ቆጰስ ።
ጸ ጸ ጠ ፤ ሠላሰኛ ። ፪/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ።
፫/ ጸመ=ጸመ ። ጸብሐ=ጠባ ። ፬/ ስሙ=ጽልመቱ ጸ ።
ጸጋ ገጹ ቀራጺ ጻድቅ ጼዴንያ ጽጌ ጸመ
ፀ ፀ ጠ ፤ ሠላሳ አንደኛ ። ፪/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ።
፫/ ፀሓይ=ፀሓይ ። ፅፍር=ጥፍር ። ፬/ ስሙ=ፀሓዩ ፀ ።
ፀሓይ ብፁዕ ሠራዊ ነፃ ዓፄ ፅዱ ያታ
ፈ ፈ ሠላሳ ኹለተኛ ። ፪/ ፈርሀ=ፈራ ።
ፈላ ፉጊ ፈና ፋታ ፈቆ ፍዳ ፎቅ
ፐ ፐ ሠላሳ ሦስተኛ ። ፪/ የጸን መሠረታዊ ተግባር ለማስወገድ በመፍጨርጨር አገ
ልግሎቱን ካውሮጳውያን ቋንቋዎች ለተወረሱ ቃላት ብቻ ለማድረግ ይጥራል።

አማርኛ ግዕዝ

ቈ ቈ ቈረ=ቈረ ። ቈስቈሰ=ቈሰቈሰ ።
ቈላ ? ቍኑ ቋት ቋ ቍስል ?

ጐ ጐ ኰ ፤ ኵሉ=ጕሉ ።
ነጐለለ? ጐሩ ኋላ ጌ ጕሉ ?

ኰ ኰ ጐ ፤ ኵስሕ=ኵስ ። ኵሉ=ጕሉ ።
ኰሰ ? ኩሩ ኳስ ኴ ኵስ ?

ገ ገ ገለተ=ገለተ ። አንገርገረ=አንገራገረ ።
ገሸ ? ጉሩ ጓዳ ዛጌ ጉዳይ ?

ማስገንዘቢያ ፩ኛ/ በምስክር ያልጸኑት ፊደላት ብቻ ባማርኛ ውስጥ ያላቸው አገልግሎት እስካኹን በተደረገው ጥናት አልተገለጸም ።
፪ኛ/ የጥያቄ ምልክት እተደረገበት ጉሉ ፊደል እንደ ጐደለ አስተውል ።

ሉ ሉ የለ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ለ ፤ ለኾኑ አናቅጽ) ። በላ=በሉ ። ጠላ=ጠሉ ። ፫/ ወይነ ተከሉ=ወይንን ተከሉ ።

መ መ የመ ካዕብ ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው መ ለኾኑ አናቅጽ) ። ሰማ=ሰሙ ። አለመ=አለሙ ። ፫/ ሕገ ፈጸሙ=ሕግን ፈጸሙ ።

ሠ ሠ የሠ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ሠ ለኾኑ አናቅጽ) ። ነገሠ=ነገሡ ። ፫/ ንጉሠ አንገሠ=ንጉሥን አነገሡ ።

ሩ ሩ የረ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ረ ለኾኑ አናቅጽ) ። መረ—መሩ ። በር—በሩ ። ፫/ መሀሩነ=አስተማሩን ።

ሱ ሱ የሰ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ሰ ለኾኑ አናቅጽ) ። መሳ—መሱ ። በሳ—በሱ ። ፫/ ብሉየ ሐደሱ=አሮጌን አደሱ

ሹ ሹ የሸ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ሸ ለኾኑ አናቅጽ) ሸሸ=ሸሹ ።

ቁ ቁ የቀ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ መድረሻቸው ቀ ለኾኑ አናቅጽ) ። በቃ—በቁ ። ነቃ—ነቁ ። ፫/ አውልዐ ሰጠቁ=ወይራን ሰነጠቁ ።

ቡ ቡ የበ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው በ ለኾኑ አናቅጽ) ። ጋለበ—ጋለቡ ። ደረበ—ደረቡ ። ፫/ ርጉበ አጽገቡ=የተራበን አጠገቡ ።

ቱ ቱ የተ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ተ ለኾኑ አናቅጽ) ። ገመተ—ገመቱ ። ፫/ መጽወቱ=መጸወቱ ።

ኑ ኑ የነ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ነ ለኾኑ አናቅጽ) ። በየነ=በየኑ ። ፫/ አድኅ ረኀኑ=አህያን ጫኑ ።
የኸ ካዕብ ። ፪/ የአንደኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ።
ለበስኩ=ለበስኹ ።

አማርኛ ግዕዝ

ዙ ዙ የዘ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ዘ ለኾኑ አናቅጽ) ። አዘዘ—አዘዙ ። ፫/ አዘዙን=አዘዙን ።

ዩ ዩ የየ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው የ ለኾኑ አናቅጽ) ። ገበየ—ገበዩ ። ፫/ ርእዩ=እዩ ።

ዱ ዱ የደ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ደ ለኾኑ አናቅጽ) ። ወደደ—ወደዱ ። ፫/ ስግዱ=ስገዱ ።

ጁ የጀ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ጀ ለኾኑ አናቅጽ) ። አበጀ—አበጁ ።

ጉ ጉ የገ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ገ ለኾኑ አናቅጽ) ። መረገ—መረጉ ። ፫/ ዕጣነ አዕረገ=ዕጣንን አሳረጉ ።

ጡ ጡ የጠ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ጠ ለኾኑ አናቅጽ) ። በለጠ—በለጡ ። ፫/ በትረ ጸበጡ=በትርን ጨበጡ (ያዙ) ።

ጩ የጨ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ጨ ለኾኑ አናቅጽ) ። ገጨ—ገጩ ።

ጹ ጹ የጸ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ጸ ለኾኑ አናቅጽ) ። ቀረጸ—ቀረጹ ። ፫/ ወልደ ገሠጹ=ልጅን ገሠጹ (ቀጡ) ።

ፉ ፉ የፈ ካዕብ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ፈ ለኾኑ አናቅጽ) ። ጸፈ—ጸፉ ። ፫/ ዘርቤተ ሰላም ነጸፉ=የፍቅር ምንጣፍን አነጠፉ ።

ሚ የመ ሣልስ ። ፪/ መድረሻቸው መ ከኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። ሳመ—ሳሚ ። ፫/ መድረሻቸው መ ከኾኑ አናቅጽ ትእዛዝ አንቀጽን መወሰኛ ። ደገመ—ድገሚ ።

ሢ የሠ ሣልስ ። ፪/ መድረሻቸው ሠ ከኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። ነገሠ—ነጋሢ ።

ሪ የረ ሣልስ ። ፪/ መድረሻቸው ራ ከኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። በራ—በሪ ። ፫/ መድረሻቸው ረ ከኾኑ አናቅጽ ትእዛዝ አንቀጽን መወሰኛ ። ሰበረ—ስበሪ ።

ሲ የሰ ሣልስ ። ፪/ መስተፃምር ። ኼደ—ሲኼድ ።

ሺ የሸ ሣልስ ። ፪/ መድረሻቸው ሠ፤ ሰ ከኾኑ አናቅጽ ትእዛዝ አንቀጽን መወሰኛ ። ነገሠ—ንገሺ ። ለበሰ—ልበሺ ።

ቂ የቀ ሣልስ ። ፪/ መድረሻቸው ቀ ከኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። በቃ—በቂ ። ፫/ መድረሻቸው ቀ ከኾኑ አናቅጽ ትእዛዝ አንቀጽን መወሰኛ ። ሰበቀ—ስበቂ ።

ቢ የበ ሣልስ ። ፪/ መድረሻቸው በ ከኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። ገባ—ገቢ ። ፫/ መድረሻቸው በ ከኾኑ አናቅጽ ትእዛዝ አንቀጽን መወሰኛ ። ገባ—ግቢ ።

አማርኛ ግዕዝ

ኪ የከ ሣልስ ። ፪/ መድረሻቸው ከ ከኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። ላከ —ላኪ ። ፫/ መድረሻቸው ከ ከኾኑ አናቅጽ ትእዛዝ አንቀጽን መወሰኛ ። ላከ—ላኪ ።

ዊ የወ ሣልስ ። ፪/ መድረሻቸው ዋ ከኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። ለዋ ለዊ ። ፫/ መድረሻቸው ወ ከኾኑ አናቅጽ ትእዛዝ አንቀጽን መወሰኛ ። ሠዋ—ሠዊ ።

ሃ የሀ ራብዕ ። ፪/ የአህያ ፡ ማናፋት ። አህያ ሲያናፋ ሃ! ሃ! ሃ! ይላል ።

ላ የለ ራብዕ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። በላ ።

ማ የመ ራብዕ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ገማ ።

ሣ የሠ ራብዕ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ነሣ ።

ራ የረ ራብዕ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ኰራ ።

ሳ የሰ ራብዕ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። በሳ ።

ሻ የሸ ራብዕ ። ፪/ የሠ ፤ ሰ ምትክ ነገሠ—መናገሻ ። ቀደሰ—መቀደሻ ። ፫/ ፈለገ። ዕቃ ይሻል ። ወንድሙን ይሻል ። ፬/ ተሰራጨ ። የበላኹት ምግብ ገና ሻ አላለልኝም ።

ቃ የቀ ራብዕ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። በቃ ። ፫/ ደረቀ ፤ ቀነበረ ። እንጀራውን ቃ አላደረገችውም ።

ባ የበ ራብዕ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ገባ ። ፫/ የበግ ጩኸት ። በጊቱ በግ ወልዳ ባ! ባ! ትላለች ።

ታ የተ ራብዕ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። መታ ።

ቻ የቸ ራብዕ ። ፪/ የተ ምትክ ። ዘመተ—ዘመቻ ።

ና ነዓ የነ ራብዕ ። ፪/ የመጣ ትእዛዝ አንቀጽ (ሦስተኛ መደብ ነጠላ) ወደ እዚኽ ና ። ፫/ ጭምር ። እርሱና እኔ መጥተን ነበር ።

ኛ የኘ ራብዕ ። ፪/ የነ ምትክ ገመነ—መግመኛ ። ፫/ ባዕድ መድረሻ ። አማራ—አማርኛ ።

አ የአ ራብዕ ። ፪/ ውጋት የያዘው ሰው ሲያቃስት የሚያሰማው ድምጽ ። አ! አ! እንዳለ አደረ ።

ካ የከ ራብዕ ። ፪/ እርባታ መሪ (ሦስተኛ መደብ ነጠላ) ቦካ ።

ዋ የወ ራብዕ ። ፪/ ዋ አለማወቅ - - - ዋ ትንካውና ! ዋ ልጅነት!
፫/ እርባታ መሪ (ሦስተኛ መደብ ነጠላ) ። ለዋ ።
፬/ አገናዛቢ ተውላጠ ስም ። ንብረትዋ ። ፭/ ማቄላመጫና ማጐላመሻ ። እናቴዋ ። ወንድሜዋ ።

ዛ የዘ ራብዕ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ገዛ ።

ጣ የጠ ራብዕ ። ፪/ የዘ ምትክ ። ገዛ—መግዣ ።

አማርኛ ግዕዝ

ያ የየ ራብዕ ። ፪/ አመልካች ። ያ ሰው ። ፫/ እርባታ አከናዋኝ ። ያመጣል ።
ዳ የደ ራብዕ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ከነዳ ።
ጃ የጀ ራብዕ ። ፪/ የደ ምትክ ። ከነዳ—መክንጃ ።
ጋ የገ ራብዕ ። ፪/ የሦስተኛ ፡ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ዘጋ ።
፫/ ዘንድ ። እኔ ጋ ነው (ጸያፍ) ።
ጣ የጠ ራብዕ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ወጣ ።
ጫ የጨ ራብዕ ። ፪/ የጠ ፤ የጸ ፀ ምትክ ። ጋጠ—መጋጫ ።
ቀረጸ—መቅረጫ ። ዐመፀ—ማመጫ ።
ፋ የፈ ራብዕ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። አለፋ ።
ቃ የቈ ራብዕ ። ፪/ ዕንጨት ወይም ዕቃ ሲሰበር የሚያሰማው ድምጽ ።
ቋ ሲል ስማኸ ። ፫/ የግር ዓይነት ።
ኻ የኰ ራብዕ ። ፪/ ተንጓጓ (ለአንደዬ) ። ጓ ሲል ሰማኸ ።
ጓ የጐ ራብዕ ። ፪/ ተንጓጓ (ለአንደዬ) ። ጓ ሲል ሰማኸ ። ፫/ የያልፈነዳ አበባ ።
ሌ የለ ሐምስ ። ፪/ አገናባቢ ። አመል—አመሌ ።
ሜ የመ ሐምስ ። ፪/ አገናባቢ ። ስም—ስሜ ።
ሚ የሠ ሐምስ ። ፪/ አገናባቢ ። ንጉሥ—ንጉሚ ።
ሬ የረ ሐምስ ። ፪/ አገናባቢ ። ሰፈር—ሰፈሬ ።
ሴ የሰ ሐምስ ። ፪/ አገናባቢ ። ነፍስ—ነፍሴ ።
ሼ የሸ ሐምስ ። ፪/ የየ ምትክ ። ጋሻ—ጋሻዬ—ጋሼ ።
ቂ የቀ ሐምስ ። ፪/ አገናባቢ ። ወርቅ—ወርቂ ።
ቴ የተ ሐምስ ። ፪/ አገናባቢ ። ቤት—ቤቴ ።
ቼ የቸ ሐምስ ። ፪/ ያንደኛ ። መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ።
በርትቼ ። ፫/ ፈረስን ኼድ ፤ ኺጂ የማያ ቃል ።
ኔ የነ ሐምስ ። ፪/ የስም መወሰኛ ። መነነ—ምናኔ ። ፫/ (አገናባቢ) ወገን—ወገኔ ።
ኜ የኘ ሐምስ ። ፪/ የነ ምትክ ። (አንደኛ መደብ ነጠላ) ። ኾነ—ኾኜ ።
ኤ የዐ ሐምስ ። ፪/ የዕብራውያን ፊደል ። ፫/ ስመ አምላክ ።
ዜ የዘ ሐምስ ። ፪/ አገናባቢ ። ጋዝ—ጓዜ ።
ዬ የየ ሐምስ ። ፪/ አገናባቢ ። ዕቃ—ዕቃዬ ። ፪/ ወሳኝ ።
ሰውዬው መጣ ። ፫/ ኃዘንን መግለጫ ።
ጌ የገ ሐምስ ። ፫/ ቅጽልን መወሰኛ ። ባለገ—ባለጌ ። ፫/ (አገናባቢ አንደኛ መደብነጠላ) ። በግ—በጌ ።
ጤ የጠ ሐምስ ። ፪/ አገናባቢ (አንደኛ መደብ ነጠላ) ። ጌጥ—ጌጤ ።
የጠ ሐምስ ። ፪/ አገናባቢ ፡ (አንደኛ መደብ ነጠላ) ። ጌጥ—ጌጤ ።
ጬ የጨ ሐምስ ። ፪/ አገናባቢ ፡ (አንደኛ ፡ መደብ ነጠላ) ። አገጭ—አገጬ ።
ጼ የጸ ሐምስ ። ፪/ አገናባብ (አንደኛ መደብ ነጠላ) ። ገጽ—ገጼ ።

አማርኛ ግዕዝ

ፈ የፈ ሐምስ ። ፪/ አገናዛቢ (አንደኛ መደብ ነጠላ) ። አፍ—አፈ ። ፫/ የዕብራውያን ፡ ፊደል ። ፬/ ስመ አምላክ ።

ም የመ ሣድስ ። ፪/ ደግሞ ። አንተም ተጣላኸኝ ። ፪/ የአሉታ ምግባር የአናቅጽ ባዕድ መድረሻ ። በላ—አልበላም ። ፫/ የምዕራፍ ከፊለ ስም ።

ስ የሰ ሣድስ ። ፪/ መስተፃምር ። እኔ ስመለስ አንተ ስትበላ መጣ ። ፫/ እን ከንን ገላጭ ። ወንድምስ አለኝ ። ሰውስ ባይፈጠር ይሻለው ነበር ። ፬/ አበ ላላጭ ። እሱስ አያምርም ።

ሸ የሸ ሣድስ ። ፪/ የሠ ፤ ሰ ፤ ምትክ ነገሠ—ነጋሸ ። ቀደሰ—ቀዳሸ ።

ብ የበ ሣድስ ። ፪/ መስተፃምር ። ብመጣ መልካም ነበር ።

ች የቸ ሣድስ ። ፪/ የተ ምትክ ። ደረተ—ደራች ።

ን የነ ሣድስ ። ፪/ የተጠቃሽ ተሳቢ ምልክት ። ጌታችንን አየኹት ። ፫/ የጥያቄ ምልክት ። ትመጣለኽን ? ፬/ የአንደኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ ። እንመጣለን ።

ኝ የኘ ሣድስ ። ፪/ የነ ምትክ ። መነነ—መናኝ ። ፫/ የአንደኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። በላኝ ። ነከሰኝ ።

እ የአ ሣድስ ። ፪/ ያንደኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ ባዕድ መነሻ ። እመጣለኹ ። ፫/ መስተዋድድ ። እቤቱ አጠገብ አገኘኹት ።

ክ የከ ሣድስ ። ፪/ የኹለተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ከ፤ ለኾኑ ፡ አናቅጽ) ። ባረከ—ባርክ ። ሰበከ—ስበክ ።

ኽ የኸ ሣድስ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። በላእከ=በላኽ ።

ው የወ ሣድስ ። ፪/ አገናዛቢ (ሦስተኛ መደብ ነጠላ) ። በሬው ሞተበት ። ፫/ ወሳኝ ። ሰውዬው መጣ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ወሰደው ።

ዥ የዠ ሣድስ ። ፪/ የዘ ምትክ ። ገዛ—ገዥ ።

ይ የየ ሣድስ ። ፪/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ አከናዋኝ ። ይምጣ ። ፫/ መድረሻቸው ለ፤ ከኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። ገደለ—ገዳይ ። ጐደለ—ጐዳይ ።

ጅ የጀ ሣድስ ። ፪/ የደ ምትክ ። አረደ—አራጅ ።

ጭ የጨ ሣድስ ። ፪/ የጠ ምትክ ። ጠጣ—ጠጭ ።

ቍ የቍዋር ከፊለ ስም ።

ሆ የሀ ሳብዕ ። ፪/ የጭፈራ አዝማች ። ሆ! እንዳሉ ዋሉ ። ሆያ ሆዬ! ።

አ የአ ሳብዕ ። ፪/ አቤቱ ፤ ሆይ እግዚ "አ" !

ዎ የወ ሳብዕ ። ፪/ አገናዛቢ (ባክብሮት) ። ሥራዎ ለዚኽ አበቃዎ ። ፫/ የኹለተኛ ። መደብ ነጠላ) እርባታ መሪ ። እለምንዎታለኹ ።

ዮ የየ ሳብዕ ። ፪/ አንቺ ። ሴትዮ ።

አማርኛ ግዕዝ

ለየ ሌለየ ነጠለ ። ገበሬው ምርትን ከግርድ ለየ ።
ከልጅ ልጅ ቢለዩ
ዓመትም አይቈዩ ።
፪/ ዐወቀ ። ሕፃኑ ፊደልን (እናቱን) ለየ ። ፫/ አወገዘ ። ሊቀ ጳጳሳቱ መናፍቁን በጴጥሮስና በጳውሎስ ሥልጣን ለየው ።

ለየ በስም መነሻ እየገባ የግልነትን የሚገልጽ ። ለየራሳችን ለየጥቅማችን ።

መሸ መስየ ቀን አልፎ ሌሊት ተተካ ። እውነትን ተናግሮ ፤ እመሸበት ያድሩዋል ። እንዴት አመሸኽ ? እንደምን አመሸኽ ?

ረጨ ረቀየ ፈነጠቀ ። ቄሱ ጠበልን ረጨ ። እጣቢውን ወደ ውጭ እርጨው ።

ሰጠ መጸወተ ። ገንዘቡን ለድኻ ሰጠ ። ፪/ ቸረ ። መጽሐፉን ለወዳጁ ሰጠ ።
፫/ አወረሰ ። እገሌ ሲሞት መላ ንብረቱን ለሚስቱ ሰጠ ።
፬/ አጋለጠ ። ይሁዳ ጌታውን አሳልፎ ሰጠ ። ፭/ እንካ አለ ።
ያልሰጡት ተቀባይ
ያልጠሩት አቤት ባይ ።

ሸሸ ሮጠ (በፍርሃት) ሙክቱ ቀበሮውን አይቶ ሸሸ ። ነገርን ሸሸ ።
የሚሸሹበት አምባ ፤ ሲሸሽ ተገኘ ።

ሸተ ሰወየ ለመብል የደረሰ ፍሬን አፈራ ። የዘረዘረው ስንዴ ሸተ ።
ወይኑ ሸተ ።

ሸጠ ሼጠ በዋጋ ለወጠ ። በጉን ሸጠ ። ሸቀጡን ሸጠ ። ይሁዳ ክርስቶስን ሸጠ ።
ግዛኝ ግዛኝ ብለው ለመሸጥ አሰበኝ ።

ቀረ ተረፈ ። ከሓምሳ ሙክቶች አንድ ብቻ ቀረ ። ከዓሥር በሽተኞች አንድ ብቻ (ከሞት) ቀረ ፪/ ከመኼድ አመለጠ ። ወደ ጦርነት ከመኼድ ቀረ ።
፫/ ተተወ ። ወይ ጋሻ
ቀድሞ ቀረኝ ።
ሥጋ ቀረ ።
ዕዳ ቀረ ።

ቀጨ ነቀለ (ከአንጓው) አክርማን ቀጨ ። ፪/ አቃወሰ ። ትራሱ አንገቱን ቀጨው
፫/ በአጭር አስቀረ ፤ ቀሠፈ ። በልጅነቱ ቀጨው ።
፬/ ሰነጠቀ (ሰውነትን) የጥቅምት ብርድ ይቀጫል ።

አማርኛ ግዕዝ

በጀ መልካም ኾነ ፤ እንኳን ። መምጣቱ በጀን ። የክርስቶስ መስቀል በጀን ።
አባት ያበጀው
ለልጅ ይበጀው ።
የሚበጀውን ፤ ባለቤት ያውቃል ። ፪/ እሺ ፤ -------በጀ! ከዚያስ በኋላ ?

ተቸ አፍታታ ፤ ተንትኖ ተናገረ ። (ከሳሽና ተከሳሽ ከተነጋገሩ በኋላ ፤ እንዲኽ ያላችኹት እንዲኽ ማለታችኹ አይደለምን ? እያሉ በተጣራ አማርኛ መጠየቅ—በዳኝነት ወይም በሽማግሌነት) እገሌ ዛሬ እንዴት አድርጎ ተቸ እባክኽ! ፪/ ነቀፈ ። መሥራቱ የለ ቁጭ ብሎ ይተቻል ። ፫/ ነውርን ስሕተትን እንከንን ጉድለትን አሳየ ተናገረ ፤ አመለከተ ። ስለ ጨዋታው የቀረበልን ትች እምብዛም አስጊ አይደለም ።

ተወ አቆመ ። ትምህርትን ተወ ። ጠጅ መጠጣትን ተወ ። ፪/ አስቀረ ።
ያምራል ብለው ከተናገሩት
ይከፋል ብለው የተዉት ።
፫/ ይቅር አለ ። ኃጢአቱን በደሉን ተወለት ። ፬/ ጣለ ። ንብረቱን ትዶ ኼደ ።

ቸረ ተኬረመ ለገሠ ። ሀብታቸውን ለድኻ ይቸራሉ ማለትን ሰማኹ ።
በሙቅ ውኃ የታጠበ ፤ በሰው ገንዘብ የቸረ ።

ቸከ ነገር ፤ ለዛና ውሳኔን አጣ ። አኹንስ ነገርኽ ቸክኝ አለው ።

ቸኸ ጥርስ እድፋም ኾነ ። ጥርሱ ቸኸ ።

ነጨ ነጸየ ነቀለ ። ጠጉሩን ነጨ (በንዴት) ፪/ መለጠ ። ፊቱን ነጨ ። ፫/ ቦተረፈ
ኧቦ ከአሀያው ቂጥ ነጨለት ።

አለ እንዲኽ ተናገረ ። ክርስቶስ ተከታዮቹንጎሉ እርስ በርሳችኁ ተፋቀሩ አለ።
ያልወለድኹት ልጅ አባቴ ቢለኝ
አፌን ዳባ ዳባ አለኝ ።
ይወደዋል ካሉ ይመክረዋል
ይወልደዋል ካሉ ይመስለዋል ።
ዝም አለ ። ቀስ አለ ። ስብርብር አለ ። እንኵትኵት አለ ።
፪/ መሰለ ፤ ተባበረ (በጣዕም) ። ማር ፤ ማር ይላል ። ወተት ወተት ይላል ።

አለ ሀለወ አልሞተም ። ይኖራል ። እንደምን አለኽ? እገሌ ሞተ? ኧረ አለ ።
፪/ አልኼደም ። እገሌ ወደ ጐንደር ኼደ? ኧረ አለ ። ፫/ ጸጋ እንዳለው
ገላጭ ፤ አስረጅ ። ቤት አለኝ ። ገንዘብ አለኝ ። መጽሐፍ አለኝ ።

አማርኛ ግዕዝ

አለ ወደ አሉታ ምግባር መለወጫ ። መኼድ—አለመኼድ ማልቀስ—አለማል ቀስ ቤት አለአጥር ፤ ሰው አለልብስ ። ቤት አለሴት ፤ ከብት አለበረት ። አለማረፍ የተርብ ቤት መቀስቀስ ።

አሸ ሐሰየ በእጁ ምርቅንና ገለባን ከፍሬ ለየ ። ያልተፈተገውን የገብስ ቆሎ ለእናቱ አሸ ። ፪/ አካል ልብስ እድፉን እንዲለቅ አፍተለተለ። በሣሙና የተመታውን ልብስ አሸ ። ፫/ ቡአ የወረደውን ፤ አካሉ የጓሎለውን የጓሎለው እንዲበተን አፍተለተለ ። የጌታውን እግር አሸ ። ፫/ አለፋ ። ቆዳን በሞራ አሸ ። ፭/ ደበደበ ። ለአምስት ኾነው አሹት ።

አበ አብ አባት ። ፪/ በትውልድ ዘርፍ ሳይኾን በዘመን ብዛት ከፍ ላለ ሰው የሚ ሰጥ የአክብሮት ስም ። አበ ፤ እንደምን ዋሉ ?

አዠ የዘንጋዳን ውኃ የመሰለ ከቀሳል ውስጥ ፈሰሰ ። የእገሌ ቀሳል አዠ ። ፪/ ጥቂት በጥቂት አፈሰሰ (አዲስ የሸክላ ዕቃ) ። አዲሱ እንስራ አዠ ።

አየ ርእየ ተመለከተ ፤ አስተዋለ ።
የጐረቤት ሌባ ፤ ቢያዩት ይስቅ
ባያዩት ይሰርቅ ።
እያየኋት የምታስቀኝ ሚስት አገባኹ ። ፪/ ተቀበለ ። መከራውን አየ ። ፫/ ተገናኘ ፤ ተጋጠመ ። በዓይነ ሥጋ ለመተያየት ያብቃን ።

አጨ ሐጸየ ለሚስትነት መርጦ ተዋዋለ ። ይኸ ጐበዝ ይኸችን ቄንጆ አጨ ። ፪/ መረጠ ። ላስተዳዳሪነት አጨው ።

ኧረ አዬ! እገሌ ኼደ ። ኧረ ።

ኧኸ እንዴ! ኧኸ! ምን ማለቱ ነው?)

ከመ ከመ እንደ ። ከመ ቅጽበተ ዓይን ። ውጉዝ ከመ አርዮስ ።

ከነ ከ—እነ አጓዳኝ አብኧር ። መስፍን ከነአሰፋ ጋራ ኼደ ።

ወደ የመድረሻ መስተዋድድ ።
ወደ ዘማ ቤት መዝለቅ
መዋፎ ጠንቅ ።

ጀለ እንከፍ ኾነ ። የእገሌ ልጅ ምነው እንዲኽ ጀለ?

ጨሰ ጨሰ በደንብ ካለመንደዱ የተነሣ ወደ ጥቍር ተናኝነት ተለወጠ ። ርጥብ ዕን ጨት ይጨሳል ። ፪/ ገመነ ። በነገሩ ጨሰ ።

ጨቀ መሬቱ ውኃ ከመጠጣቱ የተነሣ የተንቈረዘዘ ጨፈ ኾነ ። እኹንስ ሚዳው ጐሉ ጨቀ ።

አማርኛ ግዕዝ

ፈጀ፡ አቃጠለ ። እሳት ፈጀው ። ቡና ፈጀው ። ፪/ ፈጸመ ፤ አገባደደ ።
የባለጌ ልጅ መንገድ ይፈጅ
ነገር አይፈጅ ።
፫/ ገደለ ። ሕዝቡን በሽታ ፈጀው ። ፬/ ጨረሰ ። ገንዘቡን በመሸታ ፈጀው ።
ነገረ—ፈጅ=ጠበቃ ። ፍየለ—ፈጅ=የተክል ዓይነት ።

ፈጨ፡ በክክነት ፤ በክርትፍነት በጕርሶነት ፤ በስልቅነት ፤ ከግዙፍ ገላ ወደ በናኝ ገላ በወፍጮና በመጅ መሣሪያነት ፤ ለወጠ ። ሐምሳ ዳውላ እኽል በአንድ ቀን አዳር ፈጨ ።
የትም ፍጪው
ዱቄቱን አምጪው ።
እኽል ሲጠፋ ወፍጮ ይሰላል ።
እኽል ሲገኝ ወፍጮ ይመዋልጣል ።

ቄረ ቄረ፡ ቀዘቀዘ ፤ በረደ ፤ ዛሬ ምነው በኦያሌው ቄረ?

ቄየ፡ ዘገየ ምነው እገሌ ቄየ? ፪/ ጠበቀ ። ቄየኝ መጣኹ ።

ቈጨ፡ ልቡናን በላ ፤ ምነው ባደረግኹት ወይም ባላደረግኹት ኖሮ አለ ። ነገሩ ቈጨው ።

ኰሰ ሠሐሰ፡ ፍጋም ኾነ ። ይኽ ቦታ ኰሰ ። የተከመረው ቍሻሻ ኰሰ ።

ጐሸ፡ ደፈረሰ ። ምነው ይኽ ጠላ ጐሸ?

ሀሁ፡ የአማርኛ ፊደላት መጠሪያ ። ምን ትማራለኽ? ሀሁን እማራለኹ ።
ሀሁ ሳይሉ ጽሕፈት
ውል ሳይዙ ሙግት ።

መዩ፡ የዓፄ ቴዎድሮስ የፈረስ ስማቸው ። መይሳው ፤ አንበሳው እንደ ማለት ነው ።

አዉ፡ የኾሮብ ጩኸት ። ፪/ ኾሮብ ። ኦዉ መጣ ። (ለሕፃን የሚነገር)

የጁ፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ክፍለ አገር ።

ለሚ፡ የሚለማ ። ለሚ መሬት ። ለሚ አትክልት ።

ለኪ፡ የሚለካ ። መሬት ለኪ ። ዘይት ለኪ ። ልብስ ለኪ ።

ለጊ፡ የሚለጋ ኳስ ለጊ ። ሩር ለጊ ። ፪/ ጠጭ (በብዙው) ። ጠላን ለጊ ።

ለፊ፡ የሚለፋ ። ለፊ ቀጮበት ። ለፊ ሰው ።

መሪ፡ የሚመራ ። ዕዉር ሲወበራ ከመሪው ይጣላል ፤ ወይም ዘንጉን ይወረውራል ። ፪/ አለቃ ። ለመሪኽ ዓሣ ምሰል ። ፫/ ጠቋሚ ። የጠላት መሪ ነበር ። ፬/ መሪ—ጌታ=ዜማን በሥርዓት የሚያስዜም የሚመራ የሚቀነቅን ። ዜማ እንዳ

አማርኛ ግዕዝ

ይሰበር መጠበቅ የመሪጌታ ልዩ ተግባር ነው ።

ሠሪ የሚሠራ ። ሸክላ ሠሪ ። ቤተ ሠሪ ። መስተዋት ሠሪ ። ነገረ ሠሪ የገባበት ። ትዳር ፤ ቢወድም እንጂ አይደረጅም ። ወጠ ሠሪ ። ሽሩባ ሠሪ ።

ሠዊ የሚሠዋ ። ራሱን ስለ ወገኖቹና ስለ ሀገሩ ሠዊ የኾነ ፤ የክብርን አክሊል ይወርሳል ።

ረቢ የሚረባ ። ዘረ ረቢ ከኾነች ስንኳን በጅ ብር ፤ በፀም ትገዛ ።

ረቢ ረቢ መምህር ። «ረቡኒ» ?

ረኪ የሚረካ ። ጠጥቶ ረኪ ያልኾነ ይገኛልን?

ረጊ የሚረጋ ። ከአንድ ረጊ ። ረጊ ከብት ። ረጊ ወተት ።

ሰሚ የሚሰማ ። ውል ሰሚ ። ምክር ሰሚ ። አሉባልታ ሰሚ ። በደል ሰሚ ። አቤቱታ ሰሚ ። ልቅሶ ሰሚ ። ተናጋሪ ሲያመርት ፤ ሰሚ ያከማቻል ።

ሰቢ የሚሰባ ። ሰቢ ከብት ። አካሉ ሰቢ ነው ።

ሰኪ የሚሰካ ። የነገረ ሰኪን ሕንፃ ፤ ያለ ትዕግሥት የሚንደው የለም ። ሳጋ ሰኪ ። ብርጭቆ ሰኪ ። መጫሚያ ሰኪ ።

ሰጊ የሚሰጋ ። እንደ እገሊት ለንብረት ሰጊ የትም አይገኝ ። ሰጊ ናት ። ሰጊ ነው ።

ሰፊ የሚሰፋ ። ከሰፊ ቤት እራፊ አይታጣም ። መጫሚያ ሰፊ ። ኮርቻ ፡ ሰፊ ።

ሰፌ የሰፋ ። ሰፌ መጫሚያ ፤ ሰፌ ቤት ፤ ሰፌ ልብስ ፤ ሰፌ አገር ። በሰፌው ሜዳ ላይ እንደ ልብ ጉግስን መጫወት ይቻላል ። ሆደ ሰፌ ። ልበ ሰፌ ።

ቀሚ የሚቀማ ። የሰውን ገንዘብ ቀሚ ። የድኻን ሀብት ቀሚ ።

ቀሪ የሚቀር ፤ የቀረ ። ከደሞዝኽ ቀሪው ስንት ነው? ቀሪ ገንዘብ ። ቀሪ ሰው ።

ቀቢ የሚቀባ ። ቅቤ ፤ ነውር ፡ ቀቤ ። ቀለም ቀቢ ። ኖራ ቀቢ ። ዘይት ቀቢ ። ሥዕል ቀቢ ።

በሪ የሚበራ ። በሪ ጠዋፍ ። በሪ ፡ ሱራዝ ። በሪ ፋኖስ ።

በቂ የሚበቃ ። ለክርክርኽ በቂ ማስረጃን ማቅረብ ይገባኻል ። በቂ ነገር ። በቂ ነው ። በቂ ደሞዝ ። በቂ ችሎታ ። በቂ ቅጽል ። በቂ ጦር ። በቂ መሣሪያ ። በቂ ወታደር ። በቂ ሥራ ። በቂ ገንዘብ ።

ተኪ የሚተካ ። በጐደለው ተኪ ነው ። ነገርን ተኪ ። በጠፋው ተኪ ።

አማርኛ ግዕዝ

ተጊ የሚተጋ ። ለሕመምተኛ ተጊ ነው ። ለንብረት ተጊ ናት ። ለሥራ ተጊ ነው ።

ተፊ የሚተፋ ። የጐረሰውን ተፊ ። የተበደረውን ፡ ተፊ ።
ተፊው እርሱ ነው (ለቡዳ) ። አክታን ተፊ ። ጠጥቶ ተፊ ።

ነቂ የሚነቃ ። ከእንቅልፉ ነቂ ። እገሌ ነቂ ነው=ጠርጣሪ ።
መረፌ ነቂ ነው ። ነቂ እግር ።

ነኪ የሚነካ ። እንደ እገሌ ሰውን ፡ በነገር ፡ ነኪ አለ ብለኽ አትጠራጠር ።
ነኪ ኮርቻ ። የሰውን ዕቃ ነኪ ።

ነጊ የሚነጋ ። ከመከራው ጽናት የተነሣ ሌሊቱ ነጊም አልመሰለን ነበር ።

ነፊ የሚነፋ ። ጥሩንባን ነፊ ። ዋሽንትን ፡ ነፊ ። ላስቲክን ነፊ ። ኳስን ነፊ ።
ወሬን ነፊ ።

ከኪ የሚከካ ። ባቄላን ከኪ ። አተርን ከኪ ። ጠላን ፤ ጠጅን ከኪ ።

ከፊ የሚከፋ ። ከፊ መኾንዋ አይጠረጠርም ።

ወቂ የሚወቃ ። ጤፍን ወቂ ። ተልባን ወቂ ። ሰውን ወቂ ።

ወጊ የሚወጋ ። ወጊ ጦር ። እግርን ወጊ እሾኽ ። ሰውን ወጊ ዐይን አለው ።

ዘሪ የሚዘራ ።
ዘሪው ጣቴ ።
ምድሩ ያባቴ ።
እኽልን ዘሪ ። ዘሪ ሊዘራ ወጣ ።

ዘቢ የሚዘባ ። ዘቢ ምሰሶ ። ዘቢ መዝጊያ ። ዘቢ ማዕዘን ።

ዘጊ የሚዘጋ ። በርን ዘጊ ። ዘሃን ዘጊ ። ልሳን ዘጊ ።

የሚ የአናቅጽ ባዕድ መነሻ ። መጣ—የሚመጣ ። ኼደ—የሚኼድ ።

የዩ አንበሳ አይቋቋማትም የምትባል የትንሽ ትልቅ አውሬ ። ጥንት ፤ የዩን
ገዳይ ትልቅ ክብር ነበረው ።

ደሚ የሚደማ ። ደሚ ፡ አካል ። ደሚ ቍስል ።

ደቂ የሚደቃ ። ደረት ደቂ ።

ደፊ የሚደፋ ። እኽልን ደፊ ። ሰውን ደፊ ። ፈሳሽን ደፊ ።
ቍሻሻን ደፊ ።

ገሚ የሚገማ ። ገሚ ቍስል ። ገሚ ሰውነት ። ገሚ ሽቶ ።

ገሪ የሚገራ ። በቅሎን ገሪ ። ፈረስን ገሪ ። ባለጌን ገሪ ።

አማርኛ ግዕዝ

ገቢ የሚገባ ። የዕለት ገቢ ። አሽከርነት ገቢ ።
ገቢ ያፈርሳል ።
ቀዳዳ ያፈሳል ።

ገ፡ የሚገጋ ። በጥፊ ገጢ ። መጠዋን ገጢ ።

ገፊ የሚገፋ ። ዕርጎ ገፊ ። ዘመድን ገፊ ። ወሰንን ገፊ ። ፪/ ወሰን—ገፊ=የዛር ስም ።

ጠሪ የሚጠራ ። ስምን ጠሪ ። ውሻን ጠሪ ። ዋስን ጠሪ ።

ጠቂ የሚጠቃ ። ደወልን ጠቂ ።

ጠቢ የሚጠባ ። ሥጋን ጠቢ ። ጀሮ ጠቢ ። ጡትን ጠቢ ። ጣቱን ጠቢ ።

ጠፊ የሚጠፋ ። ጠፊ እሳት ። ጠፊ መብራት ። ጠፊ ቤት ። ጠፊ ንብረት ።

ፈሪ የሚፈራ ። ለፈሪ ፤ ሜዳ አይነሡም ። ፈሪ ፤ የእናቱ ልጅ ነው ። ፈሪ ፤ በገዛ ጠቡ ገላጋይ ይኾናል ። ፈሪን ፤ በውኃ ውስጥ ያልበዋል ። ዘመቻን ፈሪ ። ውኃን ፈሪ ። መግትን ፈሪ ። ሰውን ፈሪ ። ነገርን ፈሪ ።

ፈኪ የሚፈካ ። ፈኪ እኽል ።

ፈጊ የሚፈጋ ። ፈጊ ድንጋይ ። ፈጊ ማሽላ ።

ለማ፡ ለምዐ የመብቀልንና የማፍራትን ሀብት አገኘ ። የዚኽ ዓይነት ተክል እዚኽ አገር ቢለማ ፤ መልካም ነበር ። ፪/ ደረጀ ። ንብረቱ ለማ ። ፫/ ተቋቋመ ፤ ቀና ። ጠላት አጥፍቶት የነበረው ሀገር ለማ ። ፬/ ኖረ ።
ለሰው ብትል ትጠፋለኽ ።
ለእግዚአብሔር ብትል ትለማለኽ ።

ለ፡ካ ለክአ ሰፈረ ። ስንት ጠርሙስ ዘይት እንዳለው ለካ ። ፪/ ከነዳ ። ቁመቱን ለካ ።

ለ፡ካ እንዲኽ ኖሮአል! እገሌ ትላንትና ያልመጣው ለካ ታምሞ ኖሮአል ።

ለዋ በአያሌው ጠጣ ። ሰበከ ። ያንን የዳጉሳ ጠላ ለዋ ለዋና ያንዣባርረው ጀመር ።

ለዛ ያነጋገር ፤ ያሳሳቅ ፤ ያዘማመር ፤ ወዝ ፤ ጣዕም ። እገሌ ለነገሩ ለዛ የለውም ። ለዛ ቢስ ። ለዛው ደረቀ ።

ለጋ አጠነ ። ራርዋን በዱላ ፤ ኳስዋን በእግሩ መትቶ ሰማይ ለሰማይ እንድትኼድ አደረገ ። ፪/ በአያሌው ጠጣ ። ያንን ደረቅ ጠጅ ለጋ ለጋና ከግርግዳ እግር ግዳ ያላጋው ጀመር ።

አማርኛ ግዕዝ

ለጋ ጮርቃ ፤ ቃሪያ ። ለጋ ቅቤ ለሕፃን ምግብ ነው ። ለጋ ጐበዝ ። ለጋ ጨን ገር ። ለጋ ጐመን ።

ለፋ ከዱላ ፤ ከመታሸት ፤ ከመከራ የተነሣ ፤ ዛለ ፤ ለሰለሰ ፤ ለዘበ ። ቆዳው ለፋ ። መከራ ያልፋል ፤ እስኪያልፍ ግን ያለፋል ። ፪/ ጣረ ፤ ደከመ ። መድኃኒትን ለማግኘት ይለፋል ። ሊማር ይለፋል ።

ሐና ሐና ጸጋና ደስታ ። ፪/ የወላዲተ አምላክ እናት ። ፫/ የሣሙኤል እናት ። ፬/ ነቢዪት ሐና ። ፭/ ጌታችን በተወለደበት ዘመን የእስራኤላውያን ሊቀ ካህናት የነበረው (ከቀያፋ በፊት ፤ ከዘካርያስ በኋላ)

መላ ዘዴ ፤ አቅድ ፤ ብልሃት ። እገሌ መላ መምታት ያውቃል ። በመላ አመለጠ ። መላ ዐዋቂ ። ግሩም የኾነ መላ ነገረኛ ። እገሌ የጦር መላ ያውቃል ። ፪/ ማስረጃ ሳይዙ እንዲያው በጥርጣሬ ይኾናል ማለት ። እንደ ዓይነ ሥውር በመላ ይሠራል ። መላ መታ ። በመላ ዐወቀ ። በመላ የተናገረው ያዘለት ።

መሶ መልዐ እስከ አፍ ገደፉ ጢቅ አለ ። የክርስቶስ ፍቅር ልቡናን በእውነት ይመላል ። የወይኑ ዘለላ ጋን ይመላ ፤ የስንዴው ዛላ እፍኝ ይመላ ። ፪/ ጠቅላላ ፤ ድፍን መላ ንብረቱን ተወረሰ ። ፫/ በዛ ፤ ወረረ ። በአገሩ በሽታ መላ ። አገሩን አንበጣው መላው ። ፬/ ደረሰ ተፈጸመ ። ትንቢቱ መላ ። ሱባዔው መላ ። ንግርቱ መላለት ። ፭/ ጠምዝዞ አስተካከለ ። ሰዓቱን መላት ።

መራ የበቀል ጥም ። ፈንታ ። መራውን ያልተወጣ ወታደር ገደለው ።

መራ መርሐ ጠቁመ ። እገሌ ጠላቶቹን እንደሚመራብኝ የታወቀ ነው ። ፪/ ዕዉርን እጁን ፤ ጨርቁን ፤ በትሩን ይዞ ፤ ባይተዋርን ፤ ምልክት በመንገር ፤ አቅጣጫን በማመልከት ፤ መንገድን ቦታን አሳየ ። ዕዉር ለዕዉር ቢማራ ተያይዞ ገደል ። ፫/ እዘኽ ይደር ይሰንብት ብሎ አዘዘ ። ጭቃ-ሹሙ ወታደሮቹን በየመንደሩ ይመራል ። ፬/ አስተዳደረ ፤ ገዛ ። መልካም ገዥ ሕዝቡን በአማረ ሥነ ሥርዓት ይመራል ። ፭/ አወጣ ፤ አሳየ ። ሌባው የሰረቀበትን መራ ። ፮/ ቀነቀነ ፤ አሳየ ። መሪ-ጌታው መልካም ይመራል ።

መሶ መስሐ ጠገበ (ምሳን በልቶ) ። ወደ ሠርጉ የታደሙት ኹሉ መስተዋል ።

መሶ ትክክል ። አተርና ባቄላ መሶ ይለወጣል ። አንድ አሞሌ መሶ ውሰጂና ስንብጡን ፍተዪ ።

መሶ የመጽሐፈ መሳፍንት ከፊለ ስም ።

አማርኛ ግዕዝ

መቃ ሸንበቆ ፤ መለል ብሎ በመውጣቱ ፤ ለዋግንቦነት ፤ ለቀሰምነት ፤ ለመከታ ነት ፤ ለማዳወሪያነት ፤ ደግሞ ጣሪያን ለመሥሪያ የታወቀ ውስጠ ክፍት ቀርክሃን መሳይ ዕንጨት ። የመቃ ገበታ ። የመቃ ቤት ። የመቃ ጣሪያ ።

መባ መባእ ገጸ በረከት ፤ እጅ መንሻ (ለአምላክ) ። መባ ክርስቶስ ። ለቅድስት ቤተ ክር ስቲያን የማገባው መባ አለኝ ።

መ፟ታ በጥይት ፤ በዱላ ፤ እንዲሹም በሌላ መሣሪያ ፤ ወይም በረቂቅ መንፈስ ኃይል ደበደበ ። ፪/ አንኳኳ ። ደጅ ይመታል ። ፫/ አጥወለወለ ። ይሽ ደረቅ ጠጅ ልቡን መታው ። ፬/ ጠቀጠቀ ። ሸማኔው ልብሱን መታው ። ፭/ አራሰ ። ዝናብ መታው ። ፮/ ተጫወተ ። መሰንቆ ይመታል ። ፯/ ሙቀት አየለበት ። እሳት መታው ። ፀሓይ መታው ። ፰/ አጠፋ ። እሽሉን ብርድ መታው ። ፱/ ዘረፈ ። የእገሌ ጦር አገሩን መታው ። ፲/ አመመ ። ምች መታው ። ፲፩/ ተሰረረች ። ባዝራዬቱን አስመትቻት መጣኽ ። ፲፪/ ደለቀ ። ነጋሪት መታ ። ፲፫/ አሴረ ። ዓድማ መታ ። ፲፬/ ጨፈረ ። ዳንኪራ መታ ። ጮቤ መታ ። ፲፭/ አሰበ ፤ አዘጋጀ ። መላ መታ ። ፲፮/ ደቃ ። ደረትዋን መታች ። ፲፯/ ያዘ ፤ ገደለ ። አገሩን በሽታ መታው ።

መ፟ን የመጽሐፈ መጎልየ መጎልይ ከፊለ ስም

መና ባዶ ፤ ፋይዳ ቢስ ፤ መንክ ፤ ሙልጭ ። ይኽ ቦታ መና ቀረ ።

መ፟ና መና እስራኤላውያን አርባ ዓመታት ምሉ ከሰማይ እየወረደላቸው ይመገቡት የነበረ ሰማያዊ ሕብስት ።

መ፟ካ የእስላሞች ክብርት አገር ። ወደ መካ ኼዶአል ።

መዳ ድፍን ጣቃ ። አምስት መዳዎች ገዛኹ ።

መ፟ጣ መጽአ ርቀቱ አያሌ ከኾነ ቦታ ወይም አቅራቢያነት ካለው ስፍራ ተነሥቶ ወደ ሌላው ደረሰ ። እገሌ ከየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ መጣ ። በመጣበት እግሩ ተመለሰ ። ነገር መጣ ። ዝናብ መጣ ። ጦር መጣ ። ፪/ ተመለሰ ። ያየ ቢኼድ የሰማ ይመጣል ። እገሌ ከኼደበት አገር መጣ ። ፫/ ነዋሪ ኾነ ። እግዚአብሔር ይኽን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር እንዲመጣ አደረገው ፬/ ታሰበ ። አንድ አሳብ መጣብኝ ።

ሠ፟ራ ሠርሐ ተግባርን ፈጸመ ፤ አከናወነ ። ሥራውን ሠራ ። ፪/ አነፀ ። ቤትን ሠራ ። ፫/ ደነገገ ። ሕግን ሠራ ። ፬/ አደሰ ፤ ጠገነ ። የተሠበረውን ወንበር ሠራ ። ፭/ አዋሰደ ። እገሌ ነገርን መሥራት ይወዳል ።

አማርኛ ግዕዝ

ሠራ ፪/ አታለለ ። እገሌ ጉድ ሠራኝ ። ፫/ ዘበተ ፤ አፈዘ ። እገሌ እገሊትን እንደ ሸክላ እያፈረሰ ይሠራት የለም እንዴ! ፰/ አዘጋጀ ። ማዕድን ሠራ ። ፱/ ጐነጐነ ። ሽሩባን ሠራ ። ፲/ አደረገ ። ደባን ሠራ ።

ሠዋ ሦዐ አረደ (ለመሥዋዕት) በዘመነ አሪት ጠቦት ይሠዋ ነበር ። አኹን ግን በክርስቶስ መሥዋዕትነት ኹሉም ቀረ ። ፪/ ሕይወቱን አሳልፎ ሰጠ ። ክርስቶስ ራሱን ስለ ዓለሙ ሠዋ ። ወታደሩ ስለ ሀገሩ ተሠዋ ።

ረሳ ረስዐ ዘነጋ ። ለማደጎ የተሰጠው ልጅ እናቱን ረሳ ።
የወጋ ቢረሳ ።
የተወጋ አይረሳ ።
ታሞ የተነሣ እግዚአብሔርን ረሳ ።
፪/ ገደፈ ። ብላቴናው የተማረውን ኹሉ ረሳ ።
የተጻፈ ይወረሳል (ይወሳል)
በቃል ያለ ይረሳል ።

ረሳ ረብሐ የትውልድ ዘርፉ ሰፋ ፤ ዘሩ በዛ ብዙ ወለደ ። የዚኽ ሰው ዘር ረባ ።
የዚኽ ወይፈን ዘር ረባ ። ፪/ ጠቀመ ። ከንቱ መወጠር ምን ይረባል ።
ካልረባ ጉልበት ፤ እየልኝ ስሙልኝ ይሻላል ።
ካልረባ አዝማሪ ጥሬ ቃሪሚ ይሻላል ።

ረታ ረትዐ በመግት ፤ በክርክር በጦርነት በጨዋታ በውርርድ በውድድር ድልን አሸናፊነትን አገኘ ። ባላንጣውን ረታ ። መናፍቁን ረታ ። ጠላቱን ረታ ። በግ በጣ ረታ ። የተቈታቸውን ረታ ። ተቋቋሚውን ተወዳዳሪውን ረታ ።
ሐሰተኛን ሲረቱ
በወንድሙ በእኅቱ ።
በአንድ ምስክር አይረታ
በኾለት አለንጋ አይመታ ።
፪/ እንደበተ መልካም ፤ ንግግር ዐዋቂ ኾነ ። አፉ ረታ ። አንደበቱ የረታ አፈ-ጉባኤ ነው ።

ረካ ጠጥቶ ጠገበ ። ጥሙን ተወጣ ። ውኃ ጥም አቃጠለኝ ፤ አንገበገበኝ ፤ ሲል ውሎ ፤ በአንድ ብርጭቆ ጠላ ረካ ።

ረዳ ረድአ አገዘ ። ደካማ እናቱን ረዳ ። ወንድሙን ፤ አባቱን ፤ ሀገሩን ፤ ወገኑን ረዳ ።

አማርኛ ግዕዝ

በዋዛ ያልረዳ
በቁም ነገር አይረዳ ።

ረዳ ረዳ አበባው ቀይ ፤ ነጭ ፤ ብጫ ብርቱካናዊ ቀለማት ያለው ቀጋ መሳይ ፤ እሾኻም ተክል ። ጽጌረዳ ሕሊናን የሚያድስ መዓዛ አለው ።

ረጃ የአቦል ተክታይ ፤ ኹለተኛ ። አቦሉን ጠጥተን ረጃውን እንጠብቃለን ።

ረኃ ረግዐ ከፈሳሽነት ፤ ወደ ምሉ ወይም ማዕከላዊ ጥጥርነት ከቅዝቃዜ የተነሣ ተለ ወጠ ። ወተቱ ረጋ ። ፪/ ጸጥ አለ ። ሀገር ሲረጋ መጣ ። መንግሥቱ ረጋ ። ፫/ ጸና ። በሕግ ሚስቱ ረጋ ። አልጋው ረጋ ። ፬/ ጭምት ኾነ ። ይኽ ቀበ ጥባጣ ክልፍልፍ አኹንስ ረጋ ። ፭/ መናወዝን ተወ ። ይኽ ሰንጋ አሞሌን ሲያገኝ ረጋ ። ፮/ በደንብ ያልተሠራ ፤ ለመፍረስ የተቃረበ ። ረጋሽ ሥራ ፤ ለሠሪው ስም መሰበሪያ ፤ ለገዥው መክሰሪያ ነው ።

ሰላ ሰልሐ በማፍዋጨት ፤ በመሳል እንዲኹም በልዩ ልዩ ዘዴ በቀላሉ የመቍረጫን ሀብት አገኘ ። ቢላዎው ሰላ ። ፪/ ፈጸመ ። አምላክ ያለው እንጂ ሰው ያለው አይሰላም ። ፫/ ጣፈጠ ። ወጡ ሰልቶአል ። ፬/ ረታ ። አንደበቱ የሰላ ዐዋቂ እርሱን አየኹ ። ፭/ ቀና ፤ ሠለጠነ ። ወይፈኑ ሰላ ።

ሰላ ሰልጐ በጠባብ ቦታ ፤ በሠረገላ ፤ ፈሳሽ የኾነ ሳይታወቅ ገባ ። ዝናብ በማዕዘኑ በኩል ሰላ ። ፪/ ወደ ሌላው ንብረት ፤ ነገር ሳይታወቅ ገባ ። እንደ ምንም ሰላና እዚኽ ነገር ውስጥ ገባ ። ፫/ አደባ ። አዳኝ ያሰላል ።

ሰማ ሰምዐ አዳመጠ ። ዜማን ሰማ ። ፪/ ተለመነ ። አምላክ የተበዳዮችን ጩኸት ይሰማል ። ፫/ ጋለ ፤ ደመቀ ። ምጣዱ ሰማ ። ፬/ ሞከረ ። እንደ ተቅማጥ ይሰማኛል ። ውጋት መሳይ ይሰማኛል ።

ሰባ ሰብሐ ጮማ ኾነ ።
አህያ ሰባ ።
ካልተበላ ምን ረባ?
፪/ ደነደነ ። የወንበዴ ልብ ሰባ ።

ሰባ ሰብዓ ፸ ። ዓሥርና ሥሳ ሰባ ነው ።

ሰካ ሰክዐ ሻጠ ። መርፌን እግርግዳ ላይ ሰካ ። ፪/ ነገር አዋሰደ ። እገሌ ነገር ይሰካል ። ፫/ ተጫማ (በነቀፌታ) ። መጫሚያ መሳይ ሰካና ኰራ ።

ሰጋ ትልቁንም ትንሹንም አሳብ አወጣ አወረደ ። ምን ይሉኝ? ምን እኾን? ምንስ ይመጣብኝ ይኾን? ብሎ አሰበ ። እገሌ ስለ እኅቱ ሕመም ሰጋ ።

አማርኛ ግዕዝ

ሰፋ፡ ሰፍሐ ወርድና ቁመት በአያሌው አገኘ ። ቤቱ ሰፋ ። ቀዳዳው ሰፋ ። ድንቁርና እየ ጠፋ ፤ ዕውቀት እየሰፋ ፤ ይ ኮድ ዘንድ ፤ የኢትዮጵያውያን ጐሉ ተስፋና ምኞት ነው ።

ሰፋ፡ ሰፈየ ጠቀመ ። ልብስን ፤ ስልቻን ፤ ከረጢትን አገልግልን ሰፋ ።

ሸላ ምጥማጥ ፤ ድመት መሳይ ዶሮን በሊታ አውሬ ። ፪/ ልቡ ግልጽ ያልኾነ ሥዉር ፤ ድንገተኛ ፤ አድቢ ። የእግዚአብሔርን የትዕግሥቱን ብዛት በዚኽ ሸላ ይመለከትዋል ።

ሸማ ኩታን ፤ ነጠላን ፤ ጋቢን ፤ ቡሉኮን ፤ ጀኖን ልግም-በገላን ፤ ድርብን ለመሰለ ጐሉ የሚሰጥ ስም ።
ሸማ ለብሶ ስልቻ
በቅሎ ጭኖ ለብቻ
ሸማ ፤ በየፈርጁ ይለበሳል ። በለሴ ሸማ ። የቤት ሸማ ።

ሸራ ለድንኳን የሚኾን ፤ ውኃን የማያስገባ ፤ ጠንካራ ጨርቅ ። ሸራ መጫሚያ ። የውኃ ሸራ ። ሸራ ድንኳን ።

ሸና፡ ሴነ ከውኃ ጥም ፤ ወይም ከቅንጦት የተነሣ የተጠጣው መጠጥ ኩላሊት ካጣራው በኋላ ፤ አሰር አሰሩ በሕግ ረገድ ወይም ከፍርሃት የተነሣ በቁላ ቀዳዳ ወጣ ። ሽንቱን ሸና ። ፪/ ፈራ ። እገሌ እኩያው ቢገጥመው ይሸናል ።

ሸዋ በኢትዮጵያ መኻከል የሚገኝ ፤ ከዓሥራ ኹለቱ ጠቅላይ ግዛቶች አንዱ የኾነ ፤ ሰባት ትልልቅ አውራጃዎችን የያዘ ፤ የንጉሠ ነገሥቱም መናገሻ ከተማ በውስጡ የሚገኝ ጠቅላይ ግዛት ።

ሸጋ ቄንጆ (ለማሞካሸት) ። ሸጋ ልጅ ።

ቀሃ በጐንደር ውስጥ የሚገኝ ወንዝ ።
የውኃ ውኃ
ምን አለኝ ቀሃ ።

ቀላ፡ ቈሐ ደምን መሰለ ። ልጁ ቀላ ። ልብሱ ቀላ ።

ቀላ፡ ለጋ (በገና ጨዋታ) ። ጥንጉን ቀላ ።

ቀላ፡ ሰየፈ (አገዳደልን ለማሞካሸት) ። ጠላቱን በሰይፍ ቀላው ።

ቀማ፡ ቀምአ በጋይለኝነት ፤ በወንበዴነት ፤ በሽፍትነት ፤ ገንዘቡ ያልኾነውን ከሌላ ሰው ነጠቀ ። ባለጸጋ የድኻን ገንዘብ ቀማ ። ወንበዴው የመንገደኞችን ሀብት ቀማ ። ፪/ ገንዘቡ የኾነውን ወይንም ያልኾነውን በቀልድ ፤ በምር ነጠቀ ። እርሳሱን ቀማኹት ።

አማርኛ ግዕዝ

ቀሳ ሕመም እንዳይተላለፍ ለበሽተኛ የሚሠራ ልዩ ቤት (ጎጆ) ። ሕመምተኛው ሲድን ቀሳው ይቃጠላል ።

ቀ፡ ቀብዐ አነገሠ ፤ አጸደሰ ፤ መንፈሳዊ ልጅነትን አሰጠ ። እግዚአብሔር ቀብዶታል ። ሜሮንን ቀባው ። ፪/ በቅቤ ፤ በዘይት እንዲኹም በልዩ ልዩ ቅባት ወይም በፈሳሽ አለዘያም በብጥብጥ አሸ ፤ ለቀለቀ ። ቅቤን ቀባ ። ዘይትን ቀባ ። ኖራን ቀባ ። ፫/ ላከከ ። አለ ነውሬ ነውር ቀባኝ ። መዘዙን ቀባኝ ። መርዙን ቀባኝ ።

ቀባ የዱር ማር (የዋሻ የጥሻ) ። ቀባ ቄራጭ ።

ቀ፡ ቀንአ ተግመነመነ ፤ ደበነ ፤ ተበሳጨ ። ዝሙትን ከውበት ጋራ ያስተባበረች ሚስት ያለው ይቀናል ። ለሃይማኖቱ ቀና ። ፪/ ተቈጣ ፤ ቀሠፈ ። እግዚአብሔር በአምልኮቱ ይቀናል ።

ቀ፡ና ቀጥ አለ ። ጐባጣው ዕንጨት ቀና ። ፪/ ሰላ ፤ ተገረፈ ። ወይፈኑ ቀና ። ፫/ ሠመረ ፤ ሠለጠነ ። ሀገሩ ቀና ። ነገሩ ቀና ። ጕዳዬ ቀና ። ፬/ አሻረ ። መድኃኒቱ ቀናኝ ።

ቀዳ ቀድሐ ጠለቀ (በብርጭቆ በሽክና ፤ በአቦሬ ፤ በጣሳ ፈሳሽን ጠለቀ) ፤ እገሌ ውኃን ይቀዳል ። ፪/ ለቀመ ። እገሌ ጥበብን ይቀዳል ። ነገር ይቀዳል ። ፫/ ገለበጠ (ጽሑፍን) ። ድርሳነ ሚካኤልን ይቀዳል ፤ ዚቅ ይቀዳል ። ፬/ ከብዙው በክፍሉ ገለበጠ ፤ ወሰደ ። ድንን ይቀዳል ።

ቀጋ ዕንጨቱ እሾኽ ያለው ረዳን የሚመስል ፍሬው ብስል ቀይና ጣፋጭ የኾነ ቊጥቋጦ ።
የቤት ቀጋ
የሜዳ አልጋ ።

ቀጣ ቀጸአ ከብልግና ከሕግ ተላላፊነት የተነሣ ቈነጠጠ ፤ ገረፈ ፤ አሠረ ፤ ንብረቱን ወረሰ ፤ ገደለ ። ንጉሥ በሥጋ እግዚአብሔር ግን በነፍስ ይቀጣል ።

ቀ፡ ቀጽአ እያሠመረ በመጠን በመጠኑ እየቈረጠ ፤ ብራናን ወረቀትን ለጽሑፍ አዘጋጀ። ብራናን ይቀጻል ።

በሃ በረቀ ። ዕብነ በረድን ያልኾነ ነጭ ድንጋይ ።

በ፡ በልዐ ተመገበ ። እኽልን በላ ።
ሰው ፤ የወለደውን ቢስሙለት
ያቀረበውን ቢበሉለት ።
አያ ኾቦ ሳታመኻኝ ብላኝ ።

አማርኛ ግዕዝ

ከበላ ብላ
ከሰው አትጣላ ።

፪/ በዓይኑ ወጋ ። ሕፃኑን ቡዳ በላው ። ፫/ አሳዘነ ። አንጀቴን በላው ። ፬/ ውኃ ወሰደው ። ወንድሜን ውኃ በላው ። ፭/ ወጋ ። ፊቱን ፈንጣጣ በላችው ። ፮/ ደረቅ ። ዓይነ በላ ።

በራ በርሀ ተንቦገቦገ ፤ ተለኰሰ ። መብራቱ በራ ።

በራ አቆመ ። ዝናቡ በራ ። ዝናብ ሲበራ ከዋሻ ። ዝናቡ ሲበራ ከእርሱ ቤት ተነሣኹ ።

በራ በራሀ ቡዋሄ ፤ ጠጉሩ ከግንባሩ ሸሸት ሸሸት ያለ ። በራና መላጣ ልዩነታቸው ምን ድነው ?

በሳ ሸነቄረ ። መዝጊያውን በመሰርሰሪያ በሳ ።

በቃ ፍጹም ኾነ ። ድንግላዊው በቃና ሰባቱ ሰማያት ተከፍተው አየ ። ፪/ አዳረሰ ። አንዱ ጋን ጠላ ለመቶ ሰው በቃ ቢባል ያስተናባሪውን ቄጣቢነት ያስገነዝባል ። ይሙት በቃ ። ዓለም በቃኝ ። ፫/ ፈጸመ ። ሥራውን ሲያበቃ ይኼዳል ።

በዛ በዝነ ረባ ። ይኽ ዘር በዚኽ አገር በዛ ። ፪/ ከተባለው መጠን አለፈ ። ከመጫሚያው ይልቅ ጫማው በዛና አረፈ ። ፫/ አያሌ ኾነ ። ሥራ በዛብኝ ።

በዳ በድው ሰው የማይኖርበት (አሸዋማ) መሬት ፤ አገር ። የሰሐራ ምድረ በዳ ሰፊ ነው ። ምድረ በዳ ። የበዳ እንስሳ ። የበዳ አህያ ። የበዳ አውሬ ።

በዳ በግብረ ሥጋ ተገናኘ ፤ ተደመረ ።

በጋ ዝናብ የማይዘንብበት ክፍለ ዓመት ፤ የበልግ ወቅት ።
ክረምቱን የፈጀ በጋ
ዕዳውን የፈጀ ዜጋ ።

በጣ በጥሐ ስለት ባለው መሣሪያ አካልን ሰነጠቀ ፤ ቀደደ ፤ ተፈተፈ ፤ አደማ ። አካሉን በጣ ። አግሞ በጣው ።

ተሳ ተንቀሳቃሽ ነገር ከአካል ወጣ ። ሥጋው ተላ ። ወተቱ ተላ ። እበቱ ተላ ።

ተራ ጐራ ፤ ፈንታ ። ሰውጐሉ በየተራው የሞትን ጽዋ ይታደላል ። ፪/ ዝቅተኛ ። ተራ ሰው ተራ ሕዝብ ።

ተኛ ተጋደመ ። እገሌ በአልጋው ላይ ተኛ ። ፪/ አንቀላፋ ። ቢተኙ ነገር ያገኙ ፤ ቢነሡ ነገር ይረሱ ። ፫/ ተደመረ ፤ በዳ ።

አማርኛ ግዕዝ

ተኛ ወገንን የሚያመለክት ባዕድ መድረሻ ። ገበያ—ገበያተኛ ።
ሐሰት—ሐሰተኛ ።

ተካ ስለሰበረው ስለሸጠው ------ከፈለ ። ብርጭቆ ገዝቶ ተካ ።

ተጋ ተግዐ የመንፈስ ንቃት አገኘ ። ብላቴናው ለትምህርት ተጋ ።

ተፋ ተፍአ ምራቁን ፤ የጐረሰውን ወደ ውጭ አስወጣ ። ምራቁን ተፋ ። ፪/ አስታወከ ፤ አስመለሰ ። አልጠግብ ባይ ፤ ሲተፋ ያድራል ።

ነሣ ከለከለ ። ፊት ነሣው ።
ቢሰጡን እንነዳ ።
ቢነሡን እናረዳ ።
ሲበላ ለሚከሳ
ሲመክሩት ለሚረሳ ፤
ለዚያ እኽልን ለዚኽ ምክርን ንሣ ።
፪/ አሸነፈ ። ድል ነሣ ።

ነሣ አንገቱን ወደ ታች አወረደ ። እጅ ነሣ ።

ነሣ ነሥአ ወሰደ ። ጥጥ በዘይት ላይ ሲወድቅ በአካሉ ምሉ ዘይቱን ይነሣል ። ቃል ሥጋን ነሣ ።

ነቃ ነቅሐ ከእንቅልፉ ተነሣ ። ፪/ ተጋ እገሌ ለሥራ ይነቃል ።

ነቃ ነቅዐ ተሰነጠቀ ።
የቍልቋል ሣንቃ ።
በቃ ሲሉት ነቃ ።
፪/ መነጨ ። እተራራው ሥር ውኃ ነቃ ።

ነካ ዳሰሰ ፤ ዳበሰ አደረገ ። ልጁ መርዝን ነካ ። ፪/ ጐነተለ (በነገር) ።
አብ ሲነካ
ወልድ ይነካ ። ፫/ ገጠበ ። በቅሎውን መደላድሉ ነካው ። ፬/ አገኘ ።
ምን ነካኽ? ፭/ አበላሸ ። ደም ነካኝ ።

ነዛ ነዝሐ በተነ ። በምጣዱ ላይ ስንዴን ነዛ ። ፪/ ረጨ ። ደሙን ነዛው ።
፫/ ነፋ ። ጉራውን ነዛ ። ፬/ ውርድን ለዳኛ ተናገረ ። ውርድ ነዛ ።

ነዳ ነድአ አንጋጋ ። እረኛ መንጋውን ነዳ ። ፪/ በጣም አወራ (በነቀፌታ) ።
እገሌ ወሬውን ይነዳል ። ፫/ ባሪያ ፤ አገልጋይ ፤ ገዛ ።

የሰውን ይሰጥዋል ።
የገዙን ይነድዋል ።

ነኃ ነግሀ ጠባ ። ወገግ አለ ። ነህ ቀደደ ። ከነጋ ወዲያ መጣን ። ፪/ ወጣ ። የረኃቡ ዘመን አልፎ ገና እንደ ነጋ ተወለደ ።

ነሓ ነጽሐ አሸቦን መሰለ ። ልብሱ ነጣ ።
ከአፍ የወጣ
ከጥርስ የነጣ ።

ነጻ ነጽሐ ከኃጢአት ከእድፍ ተለየ ። ንስሐ ከኃጢአት ፤ ውኃ ከእድፍ ያነጻል ።

ነፃ አርነት ። ነፃ የኾነን ሕዝብ ዕውቀት ይቃኘዋል ።

ነፋ ነፍሐበ ወንፊት ጉድፍን ከተፈላጊው ለየ ። ገለባ ያለበትን እኽል በወንፊት ነፋ ። ፪/ ነዳ (ወሬን) ፡ አባ ንፋው ። ፫/ ቀበደደ ። አስጨንቆ ያዘ ። ብርዝ ሆድን ይነፋል ። ኳስን ይነፋል ። ፬/ ተጫወተ ፤ አዜመ ። መለከትን ነፋ ። ጥሩንባን ነፋ ።

አሓ ሐመየ አብጠለጠለ ። ንጉሥ በግንቡ ይታማል ።

አራ የበላውን ምግብ አሰር በቂጡ ቀዳዳ አስወጣ ። ለንጉሥ ሲኾን ወደ አን በሳ መደብ ወጡ ነው ። ለክፍተኛ ሰው ሲኾን ወደ ጓሮ ወጥተዋል ፤ ዞረ ዋል ነው ። ፪/ ተደበደበ ። ወዶ እስኪጠላ አራ ።

አሳ አባ አባት ። "አባ ፤ አባቴ ሆይ" ፪/ ለመነኰሳት የሚሰጥ የአክብሮት ስም አባ መጡ ። ፫/ ኃይለኛ ። አባ ተጫን እገሌ ። ፬/ የትል ስም መነሻ ። አባ-ጨጓሬ ። ፭/ የከብት በሽታ ስም መነሻ አባ-ሰንጋ ።

አኍ እኩያ ። ወደረኛ ፤ ብጤ ፤ መሳይ ። እገሊትን እንዳያገባ አኍው አይደለችም ።

አያ ከብላቴና በላይ ከሽማግሌ በታች ለኾነ የሚሰጥ የአክብሮት ስም ።

አጃ ስንዴን የሚመስል እኽል ። የአጃ አጥሚት ሰባራን ይጠግናል ።

አጣ ጎጥአ ደኽየ ። የሚበላው አጣ ። ገንዘብ አጣ ። ፪/ ማወቅ ተሳነው ፤ ዘነጋ ። ወንድሙን አጣው ። ፫/ ሞተበት ። ወንድሙን አጣ ። ፬/ የሌለው ኾነ ። ቅጥ አጣ ። አመል አጣ ። ፭/ ቀልበ ቢስ ። ልብዋን ያጣች ጋለሞታ ።

አፋ ከጐራዴ ሰፋ ያለ ጩቤ ። አፋ አፋቸውን ይዘው ብቅ አሉበት ።

ከሳ ከልአ ከለከለ ፤ ነጣ ። ፊት ከላው ። ፪/ አስወገደ መልኩን በመስተዋት አይቶ የዓይኑን እድፍ የጥርሱን ጉድፍ ከላ ።

አማርኛ ግዕዝ

ከሳ ተጐዳ (በአካል) የዚኽ ዓለም አሳብ ሰውነታችን ከሳ እናወፍረው ፤ ጠቈረ እናቅላው ነው ። ሕመምተኛው ከሳ ። ሕፃኑ ከሳ ።

ከካ ከረተፈ ፤ ገረደፈ ። ባቄላንና አተርን ይከካል ። ፪/ ጠጣ (በብዙ) ያንን የማሽላ ጠላ ከካ ከካና ራስ ምታት ፈንታውን ይከካው ጀመር ። ፫/ ፈለጠ ፤ መታ ። ራሴን ክፉኛ ይከካኛል ።

ከዳ ዲን ። ከዳ ያለው ማር ልብን ይመታል ።

ከዳ ኰበለለ ። ወታደር ከዳ ። አፍ ሲከዳ ከሎሌ ይብሳል ።

ከፋ ከፍአ ርኅራኄ የሌለው ኾነ ። ፪/ ጸና ። በሽታ ከፋ ። ፫/ ቸገረ ። ምን ከፋኝ ። ፬/ ጨከነ ። እርሱ ከፋብኝ ። ፭/ ተቀየመ ከፋውና ኼደ ። ፮/ተበደለ ። የተከፋ ፤ ተደፋ ።

ከፋ ከጥንት ጀምሮ የቡና ተክል ናችቶ የሚገኝበት ፤ በስተሰሜን ከወለጋና ከሸዋ በዲዴሳና በጊቤ ወንዝ ፤ በስተ ምሥራቅ ከሸዋ ፤ ከሲዳሞና ከገሙ ጎፋ በአሞ ኾርተት ፤ በስተ ደቡብ ከኬንያ ጠረፍ ፤ በምዕራብ ከሱዳን ጠረፍ ፤ የሚዋሰን ሥድስት አውራጃዎችን የያዘ ጠቅላይ ግዛት ።

ወቃ ወቅዐ ጤፍን በሙጫ ደበደበ ። ገበሬው ጤፉን ይወቃል ። ፪/ አጋኸ ወይም መከለያ ካልተገኘ የማይገታ ድብደባ ። ፫/ ጠፍ አድርጎ በታሪክ ወይም በአፍ ሰደበ ።

ወባ ንዳድ ። ወባ ታተኰሳለች ። ወባ ያዘችው ። ወባ ይዛ ታጣቅየዋለች ።

ወና ባዶ ። ወና ቤት። ወና ቤት አስታቅፋው ኼደች ። መንደሩ ጉሉ ወና ኾነ ።

ወዛ በተፈጥሮ ወይም በጥበብ ያገኘው ቅባት ፤ በፊቱ ፤ በአካሉ ቲፍ ፤ ጤም አለ ። ናጨርቲያምነቱ ቀረና ወዛ ። ፊቱ ወዛ ። እግሩ ወዛ ።

ወኃ ወግአ በጦር ። በጩቤ ፤ በእንስሳት ቀንድ ፤ በዕፀዋት እሾኽ እጠቅ ፤ እጨቅ አደረገ ። በጩቤ ወጋው ። የአቡነ ዘበሰማያት ጦር ሲወጋ እንጂ ሲወ ረወር አይታይ ። ፪/ ዘመተበት ። ይኽ መንግሥት ያንኛውን ወጋው ። ፫/ ነካ ፤ ጐነተለ ። በነገር ወጋው ። ፬/ በላ ። ፊቱን ፈንጣጣ ወጋችው ። ፭/ ተማ አለበት ። ዓይኑን ጨረር ወጋው ።

ወጣ ወጽአ አለፈ ። በፈተና ወጣ ። ፪/ ለቀቀ ። ከአዲስ አበባ ኮተማ ወጣ ። ፫/ ዘለቀ ። አቀበቱን ወጣ ። ፬/ መነጨ ። ውኃ ወጣ ። ፭/ ተቦጠለቀ ። በአፉ ደም ወጣ ። ፮/ ተነገረ ። በጋዜጣ ወጣ ። ፯/ ልማደ ሰብእ ፤ ልማደ እንስሳን ፈጸመ ። የግ ብር ውኃ ወጣች ። ሚዳ ወጣች ። እዳሪ ፤ ሰገራ ወጣ ። ፰/ ከባርነት ቀንበር ፤ ከበደለኝነት ንጹሕ ኾነ ። ነጻ ወጣ ። ፱/ ዛር ያዘው ። ዛር ወጣበት ። ፲/

አማርኛ ግዕዝ

ተግለጸ ። ጉደ_ ወጣ ። ፲፩/ ቀና ፤ ሠለጠነ ፤ ሠመረ ። ወይፈኑ ወጣለት ። ፲፪/ ተባረከ ፤ የነቃ የበቃ ኾነ ። ልጅ ወጣለት ። ፲፫/ አደገ ። ተክሉ መለል ብሎ ወጣ ። ፲፬/ ጎህ ቀደደ ። ፀሐይ ወጣች ። ፲፭/ ታየ ። ጨረቃ ወጣች ። ፲፮/ ተመረጠ ። ዕጣ ወጣለት (በት) ። ፲፯/ ተሰደደ ። ከአገሩ ወጣ ። ፲፰/ ዐረገ ። አሞራው ወደ ሰማይ ወጣ ። ፲፱/ ፈላ ፤ ብቅ አለ ። አሸን ፤ አይጥ ወጣ ። ፳/ ፈለቀ ። ጠበል ወጣ ። ፳፩/ አሰላሰለ ፤ አወጣ አወረደ ። ፳፪/ ደረሰ ። መጽሐፍ አወጣ ። ፳፫/ ያዘ ። ቂጥኝ ወጣበት ። ፳፬/ ዓይነ ደረቅ ኾነ ።

ዓይን አወጣ ። ፳፭/ አበቀለ ።

የምበላው ሳጣ

ልጇ ጥርስ አወጣ ።

ዘሃ ድር ። የሸረሪት ዘሃ ። ቤቱ ጐሉ ዘሃ በዘሃ ኾኖአልና ።

ዘማ፡ ዘማ ሸርሙጣ ፤ ቅሬ ። የዘማ አንደበት ለመጀመሪያው ከማር ይጣፍጣል ፤ ፍጻሜው ግን ከእሬት ይመርራል ።

ዘራ፡ ዘርአ በሚገባ ረገድ ዘርን በተገባ ስፍራ እንዲበቅል ጣለ ፤ በተነ ። ገበሬው ይዘራል ። ዘሪ ሊዘራ ወጣ ።

ወልዱ አይስም ፤

ዘርቶ አይከምር የለም ።

በሰኔ ካልዘሩ በጥቅምት ካልአረሙ ።

እኽል የት ይገኛል በድንበር ቢቆሙ ።

ዘቃ ቅጠል ። ዘቃ ቅቤ=በሶብላ ።

ዘባ፡ ዘብአ ቀጥ ብሎ ኖሮ ፤ አኹን ጐበጠ ፤ ጠመመ ፤ ዘበጠ ። ምሰሶው ዘባ ። ፪/ የፍርድ ሚዛን ተንሻተተ ። ፍርድ ዘባበት እንጂ ይረታ ነበር ።

ዘና ዘንጋ ፤ ችላ አለ ። ዘና ብሎ ቆሞ መታው ።

ዘካ የትንቢተ ዘካርያስ ከፊለ ስም ።

ዘጋ፡ ዘግሐ የከፈተ ተቃራኒ ። በሩን ዘጋ ። ፪/ በመሐላ ። የቅዱስ ጊዮርጊስን በር ዘጋ ። ፫/ አደራ ። ዘሃን ዘጋ ። ፬/ መናገር ተሳነው ። አንደበቱን ዘጋው ።

ዠማ ትልቅ ወንዝ ፤ ዥረት ። ፪/ ቸር ። እገሌ ዠማ ነው ።

ደላ፡ ደለወ ተመቸ ። የደላው ሙቅ ያኝካል ።

ደማ፡ ደወመ ፈሰሰ ፤ ወጣ (ለደም) ። ቍስሉ ደማ ። ውሻ አደማው ።

ደራ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ክፍለ አገር ።

አማርኛ ግዕዝ

ደራ ሞቀ (ለገበያ ፤ ለወሬ ፤ ለምጣድ) ገበያው ደራ ። ወሬ ሲደራ እናቱ ቡዳ ነች ይመጣል ። ምጣዱ ደራ ።

ደራ ዘበጠ ። የኰራ ተቃራኒ (ለቤት ውቅር) ። ይኸ ፤ የደራ ነው የኰራ?

ደቃ ደቅሐ መታ (ደረትን) ። ሞቱን ብትሰማ ደረትዋን ደቃች ።

ደባ ተንኰል ።
ደባ ራሱን ።
ስለት ድኮሱን ።
ደባ ሠራብኝ ።

ደጋ የቆላ ተቃራኒ ። የአገሩ አየር ለጤና የሚስማማ ፤ ሞቃት ያልኾነ ፤ ከፍታ ያለው ክፍለ ሀገር ፤ ዓለም ።
ከአገር ደጋ ።
ከመኝታ አልጋ ።
ወይናደጋ=ማዕከላዊ ደጋ ። ሙቀቱ ፤ በጠቅላላ የአየሩ ጠባይ ለወይን ተክል ተስማሚ የኾነ ።

ደፋ ደፍአ አፈሰሰ ፤ ከለበሰ ። ውኃን ደፋ ። ፪/ ገደለ ። እናቱን ደፋ ። ፫/ ወደቀ ። ልጇን ፤ እኔ ደፋ ልበል ። ፬/ ሜነ ፤ ተቀዳጀ ። ዘውድ ደፋ ። አክሊል ደፋ ። ፭/ አቀረቀረ ። አንገቱን ደፋ ።

ጀላ ተንጀለጀለ ሙርጥ ፤ ቁላ (ለአህያ) ።
ከገንቦ ጠላ
ከአህያ ጀላ (ቡድን) ።

ጀባ መጠቅለያ ። መጻሕፍቴን ከነጀባቸው ላክልኝ ።

ገላ አካል ፤ ሰውነት ። መላ ገላዬ ተንደበደበ ። ፪/ ፍቅር ።
ገላዬ ገላዬ እንዲባል ። ፫/ ገላ-ነክ=ውስጥ ልብስ ። ፬/ የገላ ሣሙና ።

ገማ ቄንሰ ፤ ጠነባ ፤ ሽተተ ፤ ከረፋ ። ጣት ገማ ተብሎ ተቈርጦ አይጣልም ።
ዘመዱን ያማ
ገማ ።

ገራ ገርሐ አቀና ፤ አሠለጠነ (በቅሎንና ፈረስን) ። በቅሎውን ገራ ።

ገራ አመለ ልስልስ ኾነ ። ክፋው በቅሎ ገራ ። ፪/ በቀላሉ የሚሠራ ኾነ ። ዕን ጨቱ ለፈለማ ገራ ። ጥጡ ለቡጭቅ ገራ ።

ገሳ ከቀጤማ ፤ ከእንግጫ ፤ ከመቃ ላንፋ የሚሠራ የአረኛ ዝናብ ልብስ ።

ገሳ ጣፋጭ ፍሬ ያለው በዳራገር የሚገኝ ትልቅ ዛፍ ።

ገሳ በዛ ፤ ገፋ ፤ ጦሩ እየገሳ መጣ ።

አማርኛ ግዕዝ

ገባ ቀርቀራ ። እሾኻም ብጤ የኾነ ፤ ፍሬው የሚበላ ዛፍ ።

ገሳ ገብአ ዘለቀ ። ወደ ቤት ገባ ። ፪/ ተቀጠረ ። አሽከርነት ፤ ወታደርነት ገባ ። ፫/ ሸፈተ ። ወደ አገሩ ዱር ገባ ። ፬/ ታሠረ ። ወህኒ-ቤት ገባ ። ፭/ ተለየ ። ወደ ገዳም ገባ ። ፮/ ተረዳ ። ምሥጢሩ ገባኝ ። ፯/ ተመለሰ ። ፈላሲው ፤ ስደ ተኛው ወደ ሀገሩ ገባ ። ፰/ ባለ ዕዳ ኾነ ። ዕዳ ገባ ። ፱/ ተፈጠመ ፤ ማለ ። ቃል ገባ ። ኪዳን ገባኹለት ። ፲/ ተንኰተኰተ ። ገደል ገባ ። ፲፩/ ተጸጸተ ። ንስሓ ገባ ። ፲፪/ ተገጠመ ። መዝጊያ ገባለት ። ፲፫/ ተካፈለ ። ቅርጫ ገባ ። ፲፬/ ብቻውን ተቀመጠ ። ወሸባ ገባ (የቂጥኝ መድኃኒት ሲጠጣ) ። ፲፭/ ገበረ ። ሽፍታው ገባ ። ፲፮/ ተደነጋገረ ። ግራ ገባው ። ፲፯/ ጀመረ ። ክረምት ገባ ። ወር በገባ በኾሉት ወለደች ።

ግታ አገደ ፤ አቆመ ፤ ከለከለ ።
ፈረስ ዐውቃለኹ
ስገታ እወድቃለኹ ።
፪/ ተቋቋመው ። እገሌ እገሌን ገታው ።

ግና ጌና በዓለ ልደተ ወልደ እግዚአብሔር ።
ገና በሙክቱ
ሁዳዴም በእልበቱ ።
ዘፈን ለገና
ነገር ለዋና ።
፪/ በበዓለ ልደተ ክርስቶስ ሰሞን ወጣቶችና ጐረምሶች ፤ አንድም መኻከለኞች የሚጫወቱት ጨዋታ ።
በትር ለገና
ነገር ለዋና ።
በትር ለገና
ውኃ ለዋና ።
በገና ጨዋታ
አይቈጡም ጌታ ።

ገና አልደረሰም ። የዘር ወቅት ገና ነው ። ፪/ ጀምሮአል ። ባቄላው ገና አብቦ አል ። ፫/ ይኾናል (ትንቢት) ። ገና ይመጣል ። ገና ዘንቦ ፤ ገና በርቶ ። ፬/ አልተፈጸመም ። ገና ነኝ ። ፭/ ላለፈው ኾሉተኛ ። እንደ ገና ወለደች ።

ገዛ ገዝአ መሪ ኾነ ። ግዛኝ ግዛኝ ብለው ለመሸጥ አሰበኝ ። ፪/ በዋጋ ለወጠ ። ሣህን ገዛ ። በፊን ገዛ (ባሪያን ገዛም ይባል ነበር) ።

አማርኛ ግዕዝ

ገሣ ገዝአ ፫/ ይገነዘብ ጀመር ። ልብ ገዛ ። ፭/ አሳቡን አሸነፈ ። ራሱን የገዛ በውነት ገዛኹ ይበል ። ፯/ አስታወሰ ። ልብ ገዛ ።

ገሣ ራስ ፤ እኔ ። በገዛ አረምዋ እባብ ይዛ ታስፈራራ ። በገዛ ፈቃዱ ፤ በገዛ እጁ ። በገዛ ራሴ ። በገዛ ገንዘቡ ያሻውን ያድርግ ።

ገጀ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ክፍለ አገር ።

ገጋ የዕጭ ፤ የማር መቀመጫ የኾነ እንደ እንጀራ ዓይን ያለው ።

ገጋ በጥፊ ፤ በኃይል መታ ። በጥፊ ገጋ ገጋና ለቀቀው ። ፪/ በአያሌው ጠጣ ። ያንን ጠላ ገጋ ገጋና መላ ቅዱሱ ጠፋበት ።

ገፋ ገፍአ ናጠ (ወተትን) ወተትን ገፋ ። ፪/ የመውደቅ ፤ የመንከባለል ሀብት ያለውን ከስፍራው እንዲንፍዋቀቅ (ሞከረ) አደረገ ። መኪናን ገፋ ። ፫/ በዕድል ረገድ በአንዱ ላይ የሌላው ዕድል የገዳይነትን የበዳይነትን ፤ የጨቋኝነትን እንዲኹም የመሳሰሉትን ግብሮች አገኘ ። እገሌ ዘመዶቹን ጐሉ ገፋ ። ፬/ በዛ ፤ በረከተ ። ቀኑ እየገፋ ኼደ ። ሞድዋ እየገፋ ኼደ (ለእርጉዝ) ። ፭/ አየለ ፤ በረታ ። ጠሩ እየገፋ ኼደ ። ፮/ ቻለ ። ያንን ጐሉ መከራ ያላገዳች ረዳት ገፋው ። ፯/ ተላለፈ ። ወሰን ገፋኝ ። ፰/ በደለ ። ድኻ ሲገፋ እግዚአብሔር ይክፋ ።
፱/ ፊት ነሣ (እሰው መኻከል እየሳቀለት) ።
እንዳያማኝ ጥራው
እንዳይበላ ግፋው ።

ጠላ ጠል የመጠጥ ዓይነት ። ጌሾ በውኃ ይበጠበጥና ሲፈላ ብቅልና ቂጣ ይገባል ። ከዚያም በኋላ ሲብላላ ውኃ ይመላል ። በቂ ሙቀት ባገኘ በሰባተኛው ቀን ለመጠጣት ይደርሳል ። የቤት ጠላ ። የመሸታ ጠላ ። የኃዘንተኛ ጠላ ። ብሪንጥ ጠላ=አረቂ ለማውጣት የተጠመቀ ። የጫንቃ ጠላ=ለአለቃ የበታች እየተሸከመ ያመጣ የነበረ ፤ አኹን ግን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንዲቀር አድርገውታል ። የሚሰነክል ጠላ ። ጠላ ቤት=፩/ ቤቱ ። ፪/ አለቃዱ ።
ለሴት ጠላ
ለፈረስ ቆላ ።
ነጭ ጠላ

ጠላ ጸልአ አልወደደም ። እገሌ ወንድሙን ጠላው ።

ጠማ ጸምዐ የመጠጣት ፍላጎት ተነሣሣ ። ከጠማኝ ቢሰንብት ባለርስት ይኾን ኖሮአል ።

ጠራ ጠርዐ በደብዳቤ ፤ በመልእክት ቃል በቃል ና አለ ። ሕመምተኛው ሐኪሙን ጠራ ።

አማርኛ ግዕዝ

፪/ አነበበ (የስምን መዝገብ) ። የተማሪዎችን ስም ጠራ ። ፫/ ጮኸ ። እገሌ እገሌን ይጠራል ። ፬/ አማ ። ስም ጠራ ። ፭/ ዋስ ሰጠ ። ዋስ ጠራ ። ተያዥ ጥራ ።

ጠራ ጸረየ ዅልን መሰለ ። ጠላው ጠራ ። ጠጁ ተጠራ ። ፪/ አለቀ ። (ተሸጠ) ጠጁ ተጣራ ።

ጠራ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ክፍለ አገር ።
ጠራ
ሆዱ አይጠራ ።

ጠቃ ጠቀዐ ደወለ ። መጥቅን ጠቃ ። ፪/ መታ ። መልአኩ ነጋሪቱን ጠቃ ። ፫/ ነፋ ። መልአኩ መለከቱን ጠቃ ።

ጠሳ ጠበወ መጠመጠ ። ሕፃኑ የናቱን ጡት ጠባ ። ጡጦን ጠባ ።
ጥጃ ጠባ
ከሆድ ገባ ።
፪/ ተዛመደ ። እገሌ የአቶ እገሌን ጡት ጠባ ።

ጠሳ ጸብሐ ነጋ ።
ጠባ ለኪዳን
መሸ ለቀሩባን ።
፪/ ወጣ ፤ አለፈ ። የራቡ ዘመን ጠባ ። መስከረም ጠባ ።

ጠሳ የታረደውን ከብት ብልት አወጣ ። በግ ይጠባል ።

ጠና ጸንዐ ጠነከረ ። ሕፃኑ በሥጋና በጥበብ ፤ በዕውቀትና በመንፈስም ጠና ። እግዚኤ ብሔር ያጥናዎ ። እምነቱ ጠና ። ፪/ በረታ ። ሕመሙ ጠናበት ። ራብ ጠና ። ፫/ ለመነ ፤ ተለማመጠ ። ደጅ ጠና ።

ጠዳ ፃዕደወ አማረ (በንጽሕና) ። ቤቱ ጠዳ ። ሣህኑ ጠዳ ።

ጠሳ መጠጥ ወደ ሆዱ ገባ ። ጠላን ፤ ጠጅን ፤ ጠበልን ጠጣ ። ፪/ ጭስን ወደ ሣንባው አስገባ ። ትምባሆ ጠጣ ። ፫/ አራሰ ። አትክልቱ ውኃ ጠጣ ።

ጠፉ ጠፍአ ወደመ ። መብራቱ ጠፉ ። ንብረቴ ጠፉ ። ፪/ ኰበለለ ። አሽከሬ ጠፉ ። ፫/ ሞተ ። የእገሌ ልጅ ጠፉ ። ፬/ ዘነጋ ። መልእክቱ ጠፉበት ። ፭/ ገደፈ ። የተማረው ጉሉ ጠፉበት ። ፮/ አጣ ፤ ተሳነ ። መቼ ጠፍቶት ነው የምን አለብኝ ነው እንጂ ። ፯/ ገሠሠ ። ድንግልዋን አጠፉ ። ፰/ አበላሸ ። ስም አጠፉ ። ፱/ በፍቅር ተነደፈ ። ልቡን አ ጠፉችው ። ፲/ አፈረሰ ። ውል አጠፉ ።

አማርኛ ግዕዝ

ጨሃ ጼሃ ጥርጊያ ። ጨሃ ጐዳና ። ጨሃ መንገድ ።

ጨዋ ባለጌ የአልኾነ ፤ አመለ ድልድል ። ፪/ ያልተማረ ፤ ጌታ ፤ ባለጸጋ ፤ ሀብታም ፤ የታወቀ ።
ዓሣ በወንዙ ይታረዳል
የጨዋ ልጅ በቤቱ ይፈርዳል ።

ጸና ጸንዐ ጠና ። ብላቴናው ጸና ። ፪/ ረጋ ፤ ኖረ ። በሕግ ሚስቱ ጸና ። ባለበት ጸና ። ፫/ በረታ ፤ ጠነከረ ። በእምነቱ ፤ በሃይማኖቱ ጸና ።

ጸጋ ጸጋ ስጦታ ፤ ችርነት ። ከአባታችን ከእግዚአብሔር አብ ፤ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስም ሰላምና ጸጋ ይቅርታም ለአንተ ይኹን ። ፪/ ሀብት ። ባለጸጋ= ሀብታም ።

ጸፉ ጠፍሐ አንኳኳ ። በር ይጸፉል ። ፪/ አጨበጨበ ። እጁን ይጸፉል ። ፫/ መታ ። ፊቱን ጸፋው ።

ፀዳ ፃዕደወ ጠዳ ። ፊቱን ፀዳው ። ቤቱን አፀዳው ። አፅድቶ አከራየው ።

ፈላ ፈልሐ የለስ አለ ፤ የሞቀ ፤ የተንተከተከ ፤ የተፍለቀለቀ ጎብር ስም ።
ፈላ ገነፈለ
ከመላ ጐደለ ።
፪/ ወጣ ። አሸን ፈላ ። ፫/ ተናደደ ። ደሙ ፈላ ። ፬/ ተገለጸ ። ጉድ ፈላ ።

ፈረ ፈርሀ ተንበደበደ ፤ ተንቀጠቀጠ ፤ ተርገደገደ ፤ ተንፈሰፈሰ ። እገሌ እገሌን ፈራ ። ፪/ አፈረ ። እግዚአብሔርን ከማይፈራ ወዳጅ ፤ የሚፈራ ጠላት ።
የፈሩት ይደርሳል
የጠሉት ይወርሳል ።

ፈሳ በፈቃዱ ወይም አምልጦት በእሬቡ እስትንፋስ ወጣ ። ፈሱን ፈሳ ። ፪/ ገለባ ኾነ ። ሽንኩርቱ ፈሳ ። ፫/ ድኻ መኾን ። የምትፈሳም ዶሮ የለኝ ። ፬/ ደበደበ ፤ ደቁሰ ። ወዶ እስኪ ጠላ አስፈሳው ።

ፈቃ ቄራ ። ራሱን ፈቃው ።

ፈታ ፈትሐ ለቀቀ ። እሥረኛውን ፈታ ። ፪/ አሰናበተ ። ሚስቱን ፈታ ። ፫/ ይቅር አለ ። ቄሱ (ያወገዘውን) ግዝቱን ፈታ ። ፬/ ተረጐመ ። ዕንቈቅልሽ ፈታልኝ ። ፭/ መነጋገር ቻለ ። አፍ ፈታ ። ፮/ ቦዘነ ። ሥራ ፈታ ። ፯/ በተነ ። ጠሩን በወሬ ፈታው ። ገበያ ተፈታ ። ፰/ ይቅር አሰኘ ፤ አለ ። ይፍቱኝ ። እግዚአ

አማርኛ ግዕዝ

ብሔር ይፍታ ።
ዘመድ የኾነ ቄስ
እየፈታ ያለቅስ ።
፱/ በዛ ፤ አየለ ። ደም ፈታባት ።

ፈ̇ካ ፈጋ ፤ ፈነዳ ። ማሽላ ሲቄላ ይፈካል ።

ፈ̇ጋ ተንከባለለ (በሰያፉ) ። ከዋው ድንጋይ ይፈጋል ። ናዳ እየፈጋ ይወርዳል ።
፱/ ፈነዳ ። ማሽላው ፈጋ ።

ፈጫ በክረምት ውኃ የሚኼድበት በወንዝ ግራና ቀኝ ያለ አሸዋማ መሬት ።
ፈጫ ለፈጫ ኼደ ። የዓባይን ፈጫ ብንለው ብንለው አላልቅልን አለ ።

ፈ̇ፋ ሰው እመር ብሎ ሊሻገረው የሚችል ፈረፈር ፤ መረመር ።

ቄ̇ላ በእሳት አበሰለ ። ባቄላን ፤ ስንዴን ቄላ ። ፱/ አወዛወዘ (በመለማመጥ) ውሻ
ጅራቱን ይቄላል ።

ቄ̇ራ ቄረ ብርድ ፤ ውርጭ ። ይኸን ሰሞን ቄራው ከፍቶአል ።

ቄ̇ራ በጣ ፤ ፈቃ ። የዓይኑን ቆብ ቄራው ።

ኰ̇ራ ተቤተ ። ያለ ቅጥ ኰራ ።

ኰ̇ራ ውቅሩ ያልተለመጠ ፤ ያልደራ ኾነ ። የኰራ ቤት ።

ገ̇ላ ግዙፍ ኾነ ። አጒልቶ ጻፈ ።

ገጣ ዘር ፤ ነገድ ፤ ወገን ፤ እርሱንማ ከኛ ገጣ የሚወደው ሰው የለም ።

ለሴ ጥቢኛ ፤ ሙልሙል ፤ መጠነኛ ሕብስት ። ለሴውን ፡ ሰጠኹት ።

ሐ̇ኔ ቄልማማ ገራዴ ። ሐኔ ታጥቋል ።

ሐጌ ሐጌ በዓለ እግዚአብሔር ፤ አንድም ነቢየ ጽድቅ ማለት ነው ። ፱/ የትንቢተ
ሐጌ ከፊለ ስም ።

ሐጌ አጌ ጥጥ ። ሐጌው መልካም ናችቶአል ።

መቼ ምነዬ ። መቼ መጥተኽ ኖሮአል? ፱/ ምን ጊዜ ። መቼ ትመጣለኽ? መቼ
እንደዚኽ አልኹ? መቼ ጠፋብኝ?
መቼ አነሰ=በቂ ነው ።
መቼ ጠፋብኝ=ዐውቄዋለኹ ።
መቼ አጣኹት=ዐውቄዋለኹ ።

አማርኛ ግዕዝ

መኴ ከአደንጓሬ ከፍ ያለ ነጭ ፤ ሻቦንጕርጕር ፍሬ ። በኴ ።

ሰሌ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ክፍለ አገር ።

ሰኔ ሰኔ ዓሥረኛ ወር ። የክረምት መጀመሪያ
ሰኔ መቃጠሪያ
ጎዳር መግናኛ ።
አላጋጭ ገበሬ
ይሞታል በሰኔ ።
ለሞኝ ሰኔ በጋው መስከረም ክረምቱ ።
ሰኔ
ነግ በኔ ።

ቀዬ ዱዳ ፤ በቤት አካባቢ ያለ ቦታ ። በቀዬው ሰውም እልነበረ ።

በሬ ብዕራይ ኰርማነት ተላልፎት የተቀጠቀጠ ወይፈን ። ቅንጂ በሬ ።
በሬ ስንኳ ለወገኑ በፈርስ ያጓራል ። በሬ ካራጁ ይውላል ።
በሬ ያርሳል
ምርቱን አህያ ያፍሳል ።
ለሆዳም በሬ ገለባ ያዘለታል ።

በኴ መኴ ። በኴን ያልተቸገረ አይበላውም ።

ተሚ የተማሪ ከፊለ ስም ።

ተፉ ከግንባር እስከ ማጅራት በሞላልዮሽ (ሳይላጩት) የሚቀር ጠጕር ።

ተፉ ፈጣን ። ተፉ ልጅ ።

ነዌ ነዌ መዝገበ ዐመፃ ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸ ባለጸጋ ።
ግራ ቀኝ ሳያዩ ድኻ ሲንገላታ በረኃብ ሲሞት ፤
በመብል በመጠጥ ረክቶና መስቶ ሥጋን ማስደሰት ፤
በኋላ እንደ ነዌ ኡኡ ለማለት ።

አሌ መካድ ፤ መሸፈጥ ።
አሌ ብሎ የተረታ
መኻል አገዳውን የተመታ ፤
ጉል ጊዜ አውታታ ።

አዬ ወይ! አዬ ጉድ! ይ/ ኧረ ። እገሌ መጣ ። አዬ!

ከፉ ሙላ ። እከሬው ላይ በዱላ ጠነገደው ።

አማርኛ ግዕዝ

ከሴ አይብ ውስጥ የሚገባ ትንሽ ተክል ። ፪/ ዳማ ከሴ=ሽታ ያለው ነጭ ተክል ።

ወሬ ዜና (ኾኖም ወሬ ፍሬ ቢስ መኾን ይችላል) ።
ወሬን ከባላገር
ጦርነትን ፡ ከወታደር ።
ለወሬ
የለው ፍሬ ።
ሳያጣሩ ወሬ ።
ሳይገድሉ ጮፈሬ ።
የመንደር ወሬ ። ለወሬ ንጋሪ አልተረፈም ። ወሬ ነፍሱ ። የወሬ ቋት ።
የወሬ መንዲር ። የወሬ አባት ። የአውሬ ሥጋ ለወሬ ።

ወቴ ወጥቶ አዳሬ የወታደር ከፊለ ስም ። ፪/ የቀኑልምጫ ስም ።

ወኔ የመንፈስ ጉብዝና ፤ ደገኛ አልክ ። ወኔ ቢስ ። ወኔማ ቢኖረው መቼ የአ
ባቱን ቤት ያስደፍር ኖሮአል ።

ዘኬ ኩቸሮ ። ስስ የኾነ የተስካር እንጀራ ።
ዘኬውን ሲቈጥር
አነቀው ነብር ።
ደብተራ
የዘኬ ጎተራ ።

ዘዬ አመል ፤ ሲደነግጡ ፤ ሲተክዙ የሚናገሩት አነጋገር ። እምዬ! ዘራፍ! (ፍከራ፤
ድንፋታ) ። እገሊት ብጥስ ቅንጥስ የማድረግ ዘዬ ሠልጥኖባታል ።

ዘዴ ብልሃት ። ዘዴ የማያውቅ የጦር መኰንን ወታደሮችን ያስፈጃል ።

ዘጌ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ክፍለ አገር ።

ደሬ ከሰል የሚኾን ትልቅ ዛፍ ።

ደሴ የወሎ ጠቅላይ ግዛት ዋና ከተማ ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት
አልጋ ወራሽ ፤ የልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን መኖሪያ ።

ደዌ ደዌ ሕመም ፤ በሽታ ። በክፉ ደዌ የተጠመደ ሰው ባለመድኃኒትን አጥብቆ ይሻል ።

ጀሌ መሣሪያ የሌለው ጭፍራ ። ጀሌውማ አሸን ነበር ።

ገዴ ገድዬ የአሞራ ስም ። ገዴ ገዳምነት አላት ይባላል ።

ጠኔ ጋልኛ ከእኽል እጦት የተነሣ የሚመጣ ሰመመን ።
በማለዳ እኽልን መቅመስ (ባልማስታጐል) የለመደ ። የታጣ ዕለት ጠኔ
ይጥለዋል ።

አማርኛ ግዕዝ

ጠዲ እንደ ጌሾ እጠላ ውስጥ የሚጨመር ተክል ።

ጨሌ ከፍጹምነት ያልደረሰ ልምላሜ ።

ጨሌ ምሳሌዋ ዶቃ የኾነ በሰው ላይ ታድራለች የምትባል (ረቂቅ ሥውርት ፍጥረት ።

ጨፈ ጨቀጨቅነትና ልምላሜ የማይለየው ስፍራ ።

ጨፈ ቡሉኮ ። ጨፈውን ተጐናንቦ ቁጭ ብሎአል ።

ሀይ ተው ። ሀይ ሀይ ብለን ነገሩ በርዶአል ። ፪/ አባርር ፤ ከልክል ። ከብቶቹን ሀይ በላቸው ።

ሀጭ ፉቲ ። ሀጭ ብሎ ኼደ ። ፪/ መጭ ። በቅሎዋን ሀጭ በላት ።

ሀፍ በድረግ ። ሀፍ ብሎ ተነሣ ። ፪/ ክፍት ። የሚዳው አህያ አሸታትቶ አፉን ሀፍ ግጥም አደረገ ።

ለም ጠፍ ያልኾነ ። ለም መሬት ያለው ከባለ ብዙ ወርቅ ይልቃል ። ፪/ልምላሜ ያለው ። ከብቶቹን ለም ሣር ወዳለበት እንድትወስዳቸው ።

ለስ ሞቅ ። ውኃውን ለስ አድርገው ። ለስ አለ ።

ለሽ ለጥ ። አዬ ጉድ! ይኸ እኸል ለሽ አለ ።

ለብ ለስ ። ውኃው ለብ አለ ።

ለት ሎፍ ። በየሰዉ ቤት ለት ለት ይላል ።

ለት በጎነትን የሚያመለክት የግሥ ባዕድ መድረሻ ።
መጣ—መጣለት ።

ለጥ ለሽ ፤ ትኝት ። ለጥ ብለኽ አደርኽ ።

ሐም ሐም ቀይ ። የጨርቁ ቀለም ሐም ነው ።

ሐር ሐሪር በጥቃቅን ትሎች የሚሠራ ፈትል ። ሰውም የከበረ ልብስ ከእርሱ ይሠራል ። ቀይ ሐር ። ብጫ ሐር ። ነጭ ሐር ። ውጥኔ ሐር ። ጥቍር ሐር ። ሐምራዊ ሐር ። ሰማያዊ ሐር ። አረንጓዴ ሐር ። የወይን ጠጅ ሐር ።

ሐቅ ዓረብኛ እውነት ። ለሰው ልጅ ሐቅን መናገር ክብሩ ነው ።

ሐፅ ሐፅ ፍላፃ ። የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍ ሲገባ ደረቱን ፤ ሲወጣ ባቱን እየተመለከተች በሐፀ ዝሙት ተነደፈች ።

አማርኛ ግዕዝ

መሮ ዘለለ (ለማሞካሸት) ። ፈፋውን እመር ብሎ አውጭኝ እግሬ አለ ።

መቅ ዕመቅ አዘቅት ። መቅ እንዳትወርድ (በነቀፌታ) ። ፪/ መከራ ። እምን መቅ ገብቶ ይባዝቃል?

መት መደዳ ። በመት እጨድ ። በመት ደበደበን ።

መች የሚመታ የመታ ። ሰው መች ። ሕፃን መች ። ባዝራ አስመች ።

መን የሸማኔ መሣሪያ ።

መክ የመጽሐፈ መክብብ ከፊለ ስም ።

መዝ የመጽሐፈ መዝሙራት ዘዳዊት ከፊለ ስም ።

መጅመድሐ መፍጫ ። እኽል ፤ በመጅና በወፍጮ ይፈጫል ።

መጅ ጥጥርነት ያለው እብጠት ። እጅዋ መጅ አወጣ (እንደ እጢ ኾነ) ።

መጥ የመጣ ። አዲስ መጥ ።

መጭ የሚመጣ ። ወደ እዘያኛው ዓለም ኺያጅ እንጂ ከዚያ መጭ የለም ።

መጭ አደይን የሚመስል ተክል ። ማሳው መጭ ብቻ ኾነ ። መጭ በቀለበት ።

መጭ ኺድ ፤ ኪጂ (ለበቅሎ ብቻ) ። መጭ መጭ ከሚሉት በቅሎ እግር ይሻላል ።

ሠሮ የሚሠራ ፤ የተሠራ ። ቤተ ሠር ነው ።

ሠሮ የቀና ፤ ቀጥ ያለ ፤ የሠመረ ። ማረሻው ሠር ኾኖአል ።

ረሽ የሚረሳ ።

ረሽ የአውሬ ማደኛ የኾነ ጠመንጃ ።

ረብ ረብሕ ጥቅም ፤ ፍሬ ። ረብ በሌለው ነገር ስምን ማስጠራት ፤ ካለማስተዋል የተ ነሣ የሚመጣ ስሕተት ነው ።

ረች የሚረታ ። እውነትን የያዘ የኋላ ኋላ ረች ነው ።

ረድ ረድአ ረጅ ። እርጅና የተጫጫናቸው መነኰሳት አንዳንድ ረድ አያጡም ። አርድእት ።

ረጭ የሚረጭ ። ደም ረጭ ። እጣቢ ረጭ።

ሰም ከሰፈፍ ተነጥሮ የተገኘ ። ጠዋፍ ከሰምና ከፈትል ይሠራል ። በሰም ያጣበቁት ጥርስ ፤ ቢያኝኩበት አያደቅ ቢስቁበት አያደምቅ ።

ሰስ ሚዳቋን የሚመስል ውብ አውሬ ። ሰስ እናትዋን አትረሳ ።

አማርኛ ግዕዝ

ሰቅ ቀበቶ ። ቀደምት በድግ ፤ ዘመናውያን በሰቅ ፤ ወገባቸውን ይደግፋሉ (ለወታደር) ።

ሰብ ሰብእ ሰው ። ቤተ-ሰብ ። እጅ-ሰብ አምሞታል=መድኃኒት ተደርጎበታል ። ፪/ ወገን ፤ ነገድ ። ድመት ከነብር ቤተ—ሰብ ውስጥ ይመደባል ።

ሰን ሰን ከመዳብ ወይም ከነሐስ የተሠራ ማንቄርቄሪያ ።

ሰክ ሎፍ ። እገሌ ፤ ዓሥሩ ቤት ሰክ ሰክ ይላል ።

ሸር ተንኰል ። በሰው ላይ ሸር የሚሠራን እግዚአብሔር አጥብቆ ይጠላዋል ።

ሸር ፈር ። ገበሬው አንድ ሸር አውጥቶ ፈታ ።

ሸሸ ሰው ሲሞት ከጻዕር የተነሣ የሚወጣው አር ። ሬሳ ሸሸ ።

ሸብ አበት ። ፈረሱን እዛፍ ላይ ሸብ አድርጎት መጣ ። ወገብዋን በመቀነት ሸብ አድርጋለች ።

ሸብ ሸክ ። ሸብ ሸብ አድርገሽ ቆሎ ቀዪለት ።

ሸብ ዕብነ በረድን መሳይ የዓይን መድኃኒት ።

ሸክ ሸብ ። ገብሱን ሸክ ሸክ አድርገሽ ወደ ወፍጮ ቤት ላኪው ።

ቀስ ዝግ ። ቀስ በቀስ ዕንቁላል በእግርዋ ትኼዳለች ።
ቀስ
በመቀስ ።

ቀቅ ፈንካች ለተፈንካች ፤ ገና ሳይካካሱ ለደም መተኰሻ የሚሰጠው ገንዘብ ።
የቀቅ ከፈለ ። ፪/ ዋጋ ። ቀቅ መታው ።

ቀን መዓልት ።
ቀን እንደተራዳ
ሌሊት እንደግድግዳ ።
፪/ ጊዜ ።
ቀን ከጣለው
ጐሉ ይጥለው ።
በየቀኑ ። በአንድ ቀን ። ቀን ለቀን ። ቀኑ ተዋገደ=ቀኑ መሸ ።
የበዓል ቀን ። የጸም ቀን ። የብሎት ቀን ። ሌትና ቀን ።

አማርኛ ግዕዝ

ቀኝ የግራ ተቃራኒ ። ቀኝኽን ለጸፋኽ ግራኽን አዙርለት ።

ቀይ ቀይሕ ደምን የመሰለ ። ቀይ ሰው ። ቀይ አበባ ። ቀይ ልብስ ።

ቀጥ አባጣ ፤ ጐባጣ የሌለው ። ቀጥ ያለ ምሰሶ ። ቀጥ ያለ አሳብ ።

ቀጭ የሚቀጣ ። ሕፃኑ ቀጭም የለው ።

ቀጭ ከብርድ የተነሣ የሚመጣ የአካል መሰነጣጠቅ ። ቀጭ ይዞታል ።

ቀጭ መቈርጠም ። ቆሎ መሳይ ቀጭ ቀጭ ያደርጋል ።

በር ከኹለቱ መቃንና ከጕበን ፤ ከመድረኽ መኻከል ያለው መግቢያና መውጫ ።

በክ በክ ብላሽ ፤ ከንቱ ። ዘንድሮ መሬቱ በክ ቀረ ።

በይ የሚበላ ። እኽል በይ ። ሣር በይ ።

በጅ የሚበዳ ።

በግ የፍየል ተቃራኒ ፤ የጸድቃን ምሳሌ የኾነ የቤት እንስሳ ።
በግ ከበረረ ፤
ሞኝ ካመረረ ።
በግ ፤ ባልበላሽ ትበዪኝ አለች ቀበሮ ።

በጭ የሚበጣ ።

ተስ የጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ከፊለ ስም ።

ተች የሚተች ። ነገር ተች ። ተች ነው ።

ተኝ የሚተኛ ። ተኝ ሰው ። ሴት ተኝ ።

ተግ አንጸባረቀ ። መስተዋቱ ተግ አለብኝ ።

ተግ ብልጭ ። እዚያ ማዶ ብርሃን ተግ ተግ ይላል ።

ተግ ቆም ። ዝናቡ ተግ ሲል ትኼዳለኽ ።

ተፍ ሸር ፤ ጕድ ። እገሌ አስተናባሪ ኾኖ ተፍ ተፍ ሲል ዋለ ።

ቸል ዝም ፤ ተወት ማድረግ ። እገሌ ፤ ነገሬን ቸል አለው ።
ጥጋብ ቢያምርኽ ጠላ
መግዛት ቢያምርኽ ችላ ።

አማርኛ ግዕዝ

ቸር ኄር ለጋሥ ። ቸርን በያጠብቁት ቢስ ይኾናል ።

ቸሮ እመር ። ቸር ፤ ብዬ ጉድባን እዘላለኹ ብሎ ተሰባብሮ ቀረ ።

ቸስ እጋለ ብረት ፤ ሽክላ ፤ ድንጋይ ላይ ውኃ ጠብ ሲል ቸስ ይላል ።

ቸብ ሸጥት (ለማሞካሸት) ። የአባቱን መሬት ለጠጅ መጠጫ ቸብ አደረገው ።

ቸፍ መንቀር ። አጒል ቸፍ ቸፍ ጒዳትን ያስከትላል ።

ቸፍ ሮጥ እበቅሎ ስር ቸፍ ቸፍ ይል ነበር ።

ነህ የመጽሐፈ ነህምያ ከፊለ ስም ።

ነቅ ነቅዕ መነሻ ፤ መመንጫ ቦታ ። የወንዙን ነቅ ተመልከተን መጣን ።

ነት ቀይ ቍርበት ። መልካም ነት ገዝቶ መጣ ።

ነት የቅጽሎች ባዕድ መድረሻ እየኾነ የነገርን ስም የሚያስገኝ ። ደግ—ደግነት ። ድንግል—ድንግልነት ። ፪/ የስሞች ባዕድ መድረሻ እየኾነ ሌላ ስም የሚያስገኝ ።
ሰው—ሰውነት ※

ነክ የነካ ። ገላ-ነክ=የውስጥ ልብስ ። ፪/ ውሽማ ። የሱ ነክ ነች ።

ነው የመኾን ግሥ ። ዝምታ ወርቅ ነው ፤ መናገር ብር ነው ።

ነድ ነድ በጣም ቀይ የኾነ ቀለም ። እባክኽ ነድ ግዛለት ።

ነድ የዶቃ ዓይነት ።

ነድ ጣፋጭ መዓዛ ያለው የሚጨስ ነዳጅ ።

ነግ ነግህ ነገ ። ሰው ጉሉ በሌላው ላይ መከራን ባየ ጊዜ ነግ በኔ ነው ይበል ።

ነጭ የሚነጭ ። ሥጋን ነጭ ። ፊቱን ነጭ ። ጠጒሩን ነጭ ።

ነጭ ያልቸኸውን ጥርስ ፤ በረዶን ፤ ወተትን የመሰለ ።

ነጭ ልብስ ። ፪/ ፈረንጅ ።

ነጭ ከመጣ
ነገር መጣ ።

፫/ ድኻ ። ዕድለ ነጭ ።

አማርኛ ግዕዝ

አል የቦዝ መድረሻ እየኾነ የቅርብ ኃላፊን የሚያስገኝ ።
ገባ—ገብቶ—ገብቶአል ። ፪/ አዎንታን ወደ አሉታ ለመለወጥ የግሥ መነሻ የሚኾን ። በላ—አልበላም ።

አር በቂጥ የሚወጣ የመብል አሰር ።

አስ አናቅጽን ወደ አስደራጊ ዓምድ ለመለወጥ የሚረዳ ባዕድ መነሻ ። መጣ—አስመጣ ። በሳ—አስበሳ ።

አቅ ክንድ (ለድርና ለሸማ) ። ስንት አቅ ሸማ ነው ።

አብ አብ አባት ። እግዚአብሔር አብ ፤ እግዚአብሔር ወልድ ፤ እግዚአብሔር መን ፈስ ቅዱስ ። ፪/ አበ-ምኔት=የገዳም አለቃ ። ፫/ አበ-ልጅ=የክርስትና አባት (በመንፈሳዊ ነገር አደራ የወደቀበት መጠሪያ ፤ አንድም የክርስትና አባት ከልጁ የሥጋ ወላጆች ጋራ ያለው ዝምድና መጠሪያ) ። ፬/ አበ-ነፍስ =መምህር—ንስሓ ።

አት አዎንታን ወደ አሉታ ለመለወጥ የግሥ መነሻ የሚኾን ። ኺድ—አትኺድ ።

አን አዎንታን ወደ አሉታ ለመለወጥ የሚረዳ የግሥ መነሻ ። እንብላ—አንብላ ።

አኝ ነከሰ ። እጇን አኝ አለኝ ።

አክ ማዕከላዊ ፈሳሽን በእስትንፋስ ኃይል ከጕሮሮ ቀርፎ አስወጣ ። አክ ብለው የተፉት ምራቅ ተመልሶ አይላስም ።

አዝ ዋግ (ለስንዴ) ። አዝ አጠፋው ። አዝ ተጫወተበት ።

አይ አዎንታን ወደ አሉታ የመለወጫ ባዕድ መነሻ ። ይመጣልን?—አይመጣም ።
፪/ የለም ። ትመጣለኽ? አይ! አልመጣም ።

አፍ ከአፍንጫ በታች ከአገጭ በላይ ያለ በኹለት ከንፈሮች የሚገጠም ዋሻ ። አፉ ሰፊ ነው ። አፈ-ሾሌ ። አፈ—ጭቃ ። ፪/ ንግግር ። አፍ ፈታ ። አፍና ቅብቅብ ጕል ጊዜ አያበላም ።
በአፍ ይጠፉ ።
በለፈለፉ ።
፫/ ጠርዝ ፤ ጫፍ ። የኩታው አፍ ተዛነፈ ። ፬/ ያልኾነ ነገር ያለቦታው መናገር (ሐሜት) ------) ። እጕበኛ ፊት አፉን አዳለጠው ።
፭/ ክፉ ነገር ተናግሮ የማያስቀይም ። አፈ ልስልስ ።
፮/ ጣጣቲያም ። አፈ ለብላባ ። ፯/ ወሬን የሚያበዛ ።
አፈ ዝናብ ። ፰/ ንጉሥን መስሎ የሚፈርድ (እንደራሴ) ።

አማርኛ ግዕዝ

አፈ-ንጉሥ ። ፱/ ከጠመንጃ ውስጥ የጥይት እርሳስ የምትወጣበት ። አፈ ሙዝ ። ፲/ እውስጡ ፈሳሽን ወይም ሌላ ዕቃን መያዝ የሚችል መሣሪያ በር ። ጠርሙስ ፤ ብርጭቆ ፤ ድብኝት አፍ ።
እንደ ወናፍ ፤
ኹለት አፍ ።
፲፩/ አፉ የድስትን አፍ የሚመስል ። አፈ ድስት ፤ —ብርሌ—አፍላል—ማሰሮ—ምንቸት ።

፲፪/ የጠፍርና የመጫማያ መፈያ ። አፈ-ምሳር ።
፲፫/ በስብሰባው ስላሉት ጉሉ ኾኖ የሚናገር ። አፈ-ጉባኤ ። ጴጥሮስ የሐዋርያት አፈ-ጉባኤአቸው ነበር ።
፲፬/ በአደባባይ ፤ በሸንጎ ፤ በጉባኤ መናገር የሚችል አንደበቱ የረታ ። ደኅና አፈ-መምህር ይወጣዋል ። ፲፭/ አነስተኛ ቋንቋ የጋላ አፍ ።

ከል ከል ጥቍር ፤ የኃዘን ልብስ ፤ እገሊት ምነው ከል ለበሰች? ልብስዋን ከል አገባችው ከል ነከረችው ።

ከሽ የማይጠረቃ ። ጤንነት የሌለው ሰው ጉል ጊዜ ከሽ ነው ።

ከሸ የማይረባ ። እገሌ ከሸ ነው ። ፪/ ዋዛ ። እኔ ከሸ ከሸ ወላውቅም ። ፫/ ኰቾሮ ቃ ያለ እንጀራ ፤ ቃሪያ ፤ ሲ ት ከሸ ከሸ ይላል ።

ከች ሳይታሰብ መጣ ። ስትዳራ አባትዋ ከች አሉባት ።

ከች የጨርቅ ዓይነት ። ከች ለብሶአል ።

ከፉ ወደ ላይ ወጣ ማለት ። እውነትን የያዘ ዕለት ዕለት ከፍ ከፍ ይላል ።

ወል ጋርዮሽ ።
ዳኛ የወል ፤
ምሰሶ የመኻል ።

ወር ወርኅ ጨረቃ ። ፪/ እንደ ኢትዮጵያውያን አቈጣጠር ሠላሳ ቀናት አንድ ወር ነው ። ወር በገባ በአምስት ወደ አገሩ ኼደ ። ወር ተራ ። ብዙ ወራት ኾነው ።

ወሽ ጡት እስከነግቱ (ለከብት) ። የዚኽች ላም ወሽ ትልቅ ነው ።

ወዝ ውኅዘ ፈሳሽ ። ፪/ በተፈጥሮ የሚገኝ ቅባት ። እገሌ ወዙ ጢም ፤ ቲፍ ፤ እንዳለ ነው ። ፫/ ጣዕም ። ያነጋገር ፤ ያሳሳቅ ወዝ አላት ። ለዜማው ወዝ አለው ።

አማርኛ ግዕዝ

ወይ አቤት (ለእኵያ) ። እገሌ! ወይ!

ወይ ወይም ። ወይ እኔ ፤ ወይ እርሱ መልቀቅ አለብን ። ወይ እኔ!

ወይ የማዘን ። የመገረም ፤ የማድነቅ አነጋገር ።
ወይ ጣጣ!
ምን ነገር መጣ ።
ወይ የምድር ሰው!
እኔ ዘንድ ኾነኽ ባየኽው ።
ወይ ታሪክ! ወይ ግሩም!

ወግ ደንብ ። አለቃ የወጉን አንሥቶ ቀሪውን እኩል ተካፈሉት ።
ወግ ነውና ሲዳሩ ማልቀስ ። የወግ አመጣ ። ባለ ወግ ። ፪/ ታሪክ ፤ ወሬ ።
ወግ ያዘ ። ወግ ዐዋቂ ። ወግ ጠራቂ ።

ወግ ወጋ ንድፍት ። እንደ ፡ ዓይነ ወግ አምሞታል ።

ወጥ መበያ ፤ እየተጠቀሰ የሚበላበት ። ወጥን ማን ያውቃል? ቀላዋጭ ።
ወጠ-ሠሪ=ወጥ-ቤት ። ወጥ-ቤት=ቤቱ ።
የነገር ወጡ
ማዳመጡ ።

ወጥ የወጣ ፤ ገውጡ ። ሕገ ወጥ ።

ወፍ ያፍ በክንፉ የሚበር ደማዊት ነፍስ ያለው ከአሞራ ዝቅ ያለ ፍጥረት ።
ወፍ ዛፍ አይቶ
ወታደር ቤት አይቶ ።
ወፍ እንደ አገርዋ ትጮኻለች ። ፪/ የበሽታ ዓይነት ። ወፍ አምሞታል ። ፫/ ፈጣን ። እገሌ ወፍ ነው ። ፬/ ቀጭን ፤ ክብደት የሌለው ። እገሊት ወፍ ናት ። ፭/ አዋሳጅ ። በማጀትኽ ቁጭ ብለኽ የበላይኽን አትማ የሰማይ ወፍ ምሥጢርኽን ያወጣብኻልና ።

ዘር ዘርእ ትውልድ ። ዘር ከልጓም ይጠቅሳል ። ፪/ የሚዘራ ። ዘር ትበደር ኼዳ እኽል ሲሸት መጣች ። ፫/ ልጅ ። ዘር ሳይወጣለት ቀረ ። ፬/ ክብልት ውስጥ የሚ ወጣ ፈሳሽ (ከሴት ጋራ በመደመር) እገሌ ዘሩን ታምሞአል ።

ዘብ ዘብኔ ቅራት ፤ ተረኛ ። እገሌ ዛሬ ዘብ ነው ።

ዘክ ሮጥ (ርኅቀዔታ) ። እገሌ ዘክ ዘክ ይላል ።

አማርኛ ግዕዝ

ዘው ጥልቅ ። ቤቶች እንኳ ሳይል ዘው አለ ።

ዘጥ ዘክ ። አጕል ዘጥ ዘጥ ምን ይሠራል!

ዘግ ዘፍ ፤ ውድቅ ፤ ግድም ። የባሕር ዛፍ ሲቈረጥ ወርዶ ዘግ ይላል ። ዘግ ብሎ አገኘኹት።

ዘፍ ውድቅ ። ሳያስቡው ዛፉ ዘፍ ሲል ጊዜ ነፍሱ ምንጥቅ ልትል ነበር ።

ዠር በአያሌው ፤ በብዙው አንቈረቈረ ። ሽንቱን ዠር አደረገ ።

ዠቅ ዠር ። በድንገት ዝናቡ ዠቅ አለብን ።

የም የአልተፈጸመ አድራጎትንና ትንቢታዊ ጊዜያትን የሚያመለክት የአናቅጽ ባዕድ መነሻ ። በላ—የምበላ ። ጠጣ—የምጠጣ ። መጣ—የምመጣ ።

የት ወዴት ። እገሌ የት ነው?

ደም ደም ከልብ ውስጥ ወደ አካል ውስጥ የሚሰራጭ ፈሳሽ ። ደም ተቀብቶ ዝንብ አይፈሩ ። አፈን ደም ደም አለኝ ። ደሙ ደረቀ=ከሳ ። ደም አፈታበት ። ደሙ ገባ=ተሻለው ። ደም ግባት ። የደም አብነት=የደም ጽሕፈት ። ፪/ ጥቃት ። በወንድሜ ግንባር ደም አልይበት ። ፫/ ከዕፀዋት ውስጥ የሚወጣ ፈሳሽ ። የቀ·ልቋል ደም ።

ደቅ ከዋዲያት ያነሰ ። እኽሉን በደቅ አስቀምጪው ።

ደቅ ደቅ ልጅ ፤ አሽከር ። ደቀ መዝሙር ።

ደን እልም ያለ ጫካ ፤ ዱር ። እደን ውስጥ ልዩ ልዩ አውሬ ይኖራል ።

ደዝ ዘጥ ። እገሌ አዳለጠውና እደዝ አለ ።

ደጅ ዴዴ ውጭ ። ወደ ደጅ ወጣ ።
እሠር በፍንጅ
ጣል በደጅ ።
፪/ ቦታ ፤ ስፍራ ። ደጀ—ብርሃን ። ደጀ—ሰላም ።

ደግ በጎ ። ሕመምተኛው ደግ ነው ። ፪/ ርኅሩኅ ፤ ቸር ። እገሌ ደግ ነው ። ፫/ መልካም ። ደግ ነገር ። ደግ ሥራ ። ደግ ሚስት ። ፬/ ትልቅ ፤ ዋና ። ደግ ንጉሥ ። ደጉን አምጣለት ።

ደፍ የጕበን ተነጻጻሪ ። እገሌ መቃን ተደግፎ እደፍ ላይ ቆሞአል ።

አማርኛ ግዕዝ

ደፋ ቅንቅንዋን ለማራገፍ ተርገፈገፈች ። (ለዶሮ) ዶሮዪቱ ደፍ ደፍ አለች ። ፪/ መንጐዳጐድ ። እጓዳ ደፍ ደፍ ትላለች ።

ጀር በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የደብረ ሊባኖስ አቅራቢያ የኾነ ገዳም ።

ጀብ ቸብ ። በጨንገር መሳይ ጀብ ጀብ አደረገው ።

ገል የሸክላ ስባሪ ። በገል እሳት ጭራ ኼደች ።

ገር የዋህ ፤ የማይጨክን ። ገርን ልጅ እናቱ አትወደውም ።

ገር ጠንካራ ያልኾነ ። ገር ዕንጨት ነው (ለመፍለጥ አያውክምና) ።

ገብ የገባ ። ወዶ ገብ ። ግብረ—ገብ ። ውኃ—ገብ መሬት አለኝ ። ድረ—ገብ=ፈት ።

ገች የገታ ። በቅሎን ገች ። አሳብን ገች ።

ገዥ የሚገዛ ። እኽልን ፤ ዕቃን ገዥ ። ፪/ መሪ ፤ አስተዳዳሪ ። አገረ-ገዥ ።

ገድ መልካም አጋጣሚ ። በጠዋት መቶ ብር ማግኘት እጅግ በጣም ጥሩ ገድ ነው ። ገደ ቢስ ክፉ ገድ ። መልካም ገድ ።

ገጭ ኹለት አካላት በኃይል ሲገናኙ ራሱን በሩርዙም ገጭ አደረገው ።

ገጽ ገጽ ፊት ። ገጽዋ አጉማዶ መሳይ ነው ። ፪/ የመጽሐፍ ቅጠል ፤ መልክ ። መጽሐፉ ስንት ገጾች አሉት? አንድ ቅጠል ፤ ድንዳኔው የታሰበ እንደኾን አራት ገጾች አሉት ቢባል ያስኼዳል ።

ጠል ጠል ጤዛ ፤ ውርጭ ። ጠል ወርዶበታል ።

ጠር አዲስ ጨርቅ ሲቀደድ የሚያሰማው ድምፅ ።

ጠር ጸር ጠላት ። እገሌ ምነው ጠር ኾነብኝ ።

ጠሸ (ባቄላና አተር) ፈነዳ ። ባቄላ ሲንዶሸዶሸ ጠሸ ጠሸ ይላል ።

ጠቅ ውግት ። በነገር እጠቅ አደረገው ። ውጋት ጠቅ ጠቅ ያደርገኛል ።

ጠብ ጥል ። ጠብ የሻ መኰንን የዶሮ ሻኛ አምጡ ይላል ።

ጠብ ዱብ ። ዝናብ ጠብ ካለ መሬቱ ጭቃ ይኾናል ። በመስኮት ጠብ ብሎ ኼደ ። ፪/ መታ (አንደዱም ሳይስት) ። ተኳሹ ወፊትዋን ጠብ አደረጋት ።

ጠኝ የሚጠና ። ደጀ-ጠኝ ። እገሌ ደጀ-ጠኝ ነው ።

ጠጅ ከማርና ከጌሾ በውኃ ተበጥብጦ የሚሠራ መጠጥ ።
ጠጅ በብርሌ
ነገር በምሳሌ ።

ጠፍ ለም ያልኾነ ። የእገሌ መሬት ጠፍ ነው ።

አማርኛ ግዕዝ

ጠፍ ሙልጭ (ለስድብ) ። እገሌ ጠፍ አድርጎ ሰደበኝ ።

ጨቅ ውግት ፤ ጠቅ ። እገሌ እገሌን በመርፌ ጨቅ አደረገው ።

ጨው በአንኳርነት ያለ ልመደው ፤ አሞሌ ፤ እየለየ፤ ጋንፋራ ። ጨው ፤ ለራስኽ ስትል ጣፍጥ አለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉኻል ።

ፈር ሸር ። ገበሬው ፈር አወጣ ።

ፈስ በእሬብ ውስጥ የሚወጣ ግማት ያለው እስትንፋስ ።

ፈቅ እልፍ ። ወደዚያ ፈቅ በል ። ፈቅ ብለሽ ተኚ ።

ፈት የሌለው ። ሥራ-ፈት ። እገሌ ሥራ-ፈት ነው ።

ፈት ድረ-ገብ ፤ ጋለሞታ ። እገሊት ፈት ናት ።

ፈጅ ገዳይ ፤ ጨራሽ ። አህያ-ፈጅ ። እኽል ፈጅ-ጎሉ ተሰብስቦ!
፪/ ፈጻሚ ። ነገረ-ፈጅ=ጠበቃ ።

ለኮ ጋልኛ እልባብ ላይ የተዋደደ የበቅሎ ፤ የፈረስ መሳቢያ ።

መሮ መርሀ መፈልፈያ ። አናጢው መሮን ይዞአል ።

መቶ ምዕት ፪ ። ሰማኒያና ኻያ መቶ ነው ።

ሰኞ ሰኑይ በእሑድና በማክሰኞ መኻከል ያለ ቀን ፤ ትርጓሜው ኹለተኛ ማለት ነው ።

ሸፎ ሸፋፋ ።
ሸፎ ገመዳ
ቢሞት አይገመዳ
ቢሰበር ዕዳ ።

ቀፎ ቀፎ የንብ ማኖሪያ ። ከዚያ ቀፎ ውስጥ ፤ ንብ ወልዶ ኼደ ።

በሶ የታመሰ ገብስ ዱቄት ። የመንገደኞች ስንቅ በሶ ነው ።

ተኅ ኺድ! ተመለስ! (ለበሬ) ገበሬው በሬውን ተኅ ተኅ ሲል ።
ያስደንቅ ነበር ።

ነዶ ገበሬ ሲያጭድ በአንድ እጅ ምሉ ሲኾን የሚያሥረው እሥር ።

ነዶ ነድዶ በማጋነን ቍጭትን መግለጫ ። ወይ ነዶ!

አሮ አራም (ለስድብ) ።

አቦ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ። ፪/ ዕድል=አቦ-ሰጡኝ ፤ አቦ-ሰጥ=የአቦ ስጠታ ።

አቶ አቤቶ የአክብሮት ስም ። አቶ እገሌ መጡ ። አቤቶ=አበ-ቤት

አኛ የማይታኘክ ፤ ጥብቅ ፤ እንደ ሥር የኾነ ሥጋ ። ይኸ ሥጋ አኛ ነው ።

አማርኛ ግዕዝ

አዞ በውኃ ውስጥ የምትገኝ አውሬ ፤ ብዙውን ጊዜያት በአንስታይ ጾታ ትጠራለች ።

ከሎ ጋልኛ ክልክል መስክ ። እገሌ ለከብቶቹ ከሎ ገዝቶአል ።

ወሎ በሰሜን ትግሬ ፤ በምሥራቅ ኤርትራ ፤ የፈረንሳይ ሱማሌ ፤ በደቡብ ሐረርጌና ሸዋ ፤ በምዕራብ ጐጃምና በጌምድር የሚዋሰኑት ፤ ስምንት አውራጃዎችን የያዘ ጠቅላይ ግዛት ነው ።

ወዮ ልቅሶ ። እገሌ ሞተ ። ወዮ! ሞተ? ፪/ ይብላኝ ። «ወዮላችኁ እናንት የዕውሮች መሪዎች ፤ ትንኝን የምታጠሩ ፤ ግመልን የምትውጡ» ።

ወዶ ግሩም ፤ ድንቅ (ለማፌዝ) ።

ደቦ ጅጌ ፤ ወበራ ። እገሌ የእኽል አጨዳ ደቦ አለበት ።

ገቦ ኾነ ብለው ሳይዘሩት ፤ ሲታጨድ በመርገፉ የበቀለ ገቦ ይባላል ።

ኡኡ እሪ ። ትላንትና አንተ ቤት ኡኡ ሲባል ነበር ።

ኡኹ ሳለ ። ኡኹ ኡኹ አለ ። በርበሬ ኡኹ ኡኹ ያሰኛል ።

ሙጢ ሹል ። አፍዋ ሙጢ ነው ። ፪/ አፈኛ ። ምን ያለችው ሙጢ አፍ ነች እባክኽ!

ሱቲ ልዩ ልዩ ቀለማት ያለው የጨርቅ ዓይነት ። የአምስት ብር ሱቲ አለብኝ ።

ቡቺ ኩቲ ፤ ውሻን የመጥሪያ ቃል ።

ኩቲ ቡቺ ፤ ውሻን የመጥሪያ ቃል ።
ሃይማኖት ታረደ ደሙን ኩቲ ላሰው
እንግዲህ ሆድ ለሆድ አልተገናኘም ሰው ።

ጡሊ ጦልጥዋላ ። ምን ያለው ጡሊ ነው እባክኽ!

ጡዚ ጦዝጥዋዛ ። እገሌ ጡዚ ነው ።

ፉሲ ፈሳም ፤ ፈሪ ። እገሌ የፉሲ ፉሲ ነው ።

ፉቲ እግሬ አውጭኝ አለ ። ተኵስ ሲሰማ ጊዜ ፉቲ አለ ።

ሉያ ሉያ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ። ሃሌ ሉያ ።

ሉቃ የሉቃስ ወንጌል ከፊለ ስም ።

ሙላ የአካል ክፍል ። እወገብ አጠገብ ያለ የታፋ (የእግር) መገናኛ ።

ሙና ባለማደጉ ውበት ያልተለየው ፤ መልካም ፤ ባለመውለድ ፤ ባለማፍራት ገና ጨቅላ መስሎ መታየት ።
ሙናዬ ሙናዬ
አትርሽኝ ገላዬ ።

ሙያ መቀያ ሰው ፤ ማወቅ የሚገባው ተግባር ። እገሊት ባለሙያ ናት ።
እገሌ የጦር ሙያ ያውቃል ። ፪/ ጅግንነት ። ይኽ ወታደር እጅግ በጣም ጥሩ ሙያ አለው ።

አማርኛ ግዕዝ

ሉ፞ጫ እጅግ በጣም ዝልፍልፍ ጠጕር ።
ጠጕረ ሉ፞ጫ
ዓይነ መጭ፞ማጫ ።

መ፞ዳ ከሰፊ እጅ ፤ ጭብጥ ፤ ቡጢ ከፍ የሚል የሥጋ ቍራጭ የዳቦ ቍራሽ ።
በተቈጣ ፤ ባመሸ ፤ በሰከረ ቍጥር መ፞ዳ መ፞ዳ ሥጋ ከአካሉ እየተነጣ እን
ዴት ልኑር! አለች ።

መ፞ጃ በክረምት ወራት ፤ አንድም ዝናብ ሲያካፋ የሚበቅል ፤ ከብት ሲበላው
ተቅማጥ የሚ፞ኾን ሣር ። ለጥጃው መ፞ጃ አትስጡት ።

መ፞ጋ ከሲታ ፤ ሞጋጋ ። እገሊት ምነው መ፞ጋዋ ወጣ?

መ፞ጣ ጋልኛ ፈንዛ ፤ ጭራው ነጭ የሆነ በሬ ። ይ፞ኸ መ፞ጣ በሬ ባለመ፞ያ ነው ።

ሹ፞ካ የመን፞ሽ ቅርጽ ያለው ምግብን በእርሱ ወግቶ ለመቍረጥ አንድም ወደ
አፍ ለማቅረብ የሚያገለግል ፤ በመጠን ቢላዎን የሚወዳደር መሣሪያ ።

ቁላ ጀ፞ላ ፤ መ፞ርጥ ።

ቁራ ድፍን ጥቍር ፤ አንድም እልቡ ላይ ነጭ የጣለበት አሞራ ።

ቁና፞ የእ፞ኽል መስፈሪያ ። ኻያ ቁና አንድ ዳውላ ነው ።

ቡሃ ቆረቆርን የሚመስል ጠጕርን የሚመልጥ በ፞ሽታ ።

ቡ፞ላ ደማቅ ቀይ ያል፞ኾነ ፤ ወደዳለቻ፞ነት የሚጠጋ የቀለም ዓይነት ።

ቡና፞ ፍሬው ፤ ተቈልቶ ተወቅጦ ተፈልቶ የሚጠጣ ዛፍ ።
ቡናና ፍቅር በትዝ፞ታ ነው ።
የቡና ስባቱ
መፋጀ፞ቱ ።
የቡና ቀዝ፞ቃዛ
የሹ፞ም ፈዛዛ ።

ቡአ ጋልኛ የትርፍ አንጀት መታ፞ወክ ፤ የወረደ ። እገሊት ቡአ ወርዶአታል ።

ቡዳ በመመልከት ቀልቡ ያረፈበትን ሰው ፤ እንስሳ በዓይኑ የመውጋት ችሎታ
ያለው ሰው ።

ኩ፞ታ ኻ፞ለት የተነባበሩ ነጠላዎች ። ፪/ እኩሌታ ። ልማ—በገላ አራት ነጠላዎች
ሲ፞ኾን ኩ፞ታ ግን ኻ፞ለት ነጠላዎች ነው ።

ዙሃ ጠገራ ። ዙሃውን አምጣልኝ ።

አማርኛ ግዕዝ

ገዥዋ ዘግ ፤ ዘፍ ። አዞረውና ወርዶ ገዥዋ አለ ። ፪/ ገር ። ውኃውን ገዥዋ አደረገው
ዱላ በትር ። እገሌ ዱላ አለው ። ፪/ መደባደብ ። እገሌ ዱላ ይወዳል ። ዱለኛ ነው ።
ዱባ በምድር ላይ ሐረጉ የሚሳብ ፤ ቅልን የሚመስል ፤ ለመብል የሚኾን ተክል ።
፪/ ወፍራም ። እገሌ ዱባ ነው ።
ዱታ እንዲኽ ለምን ኾነ ወይም ለምን ሳይኾን ቀረ ፤ አንድም እንዲኽ ይኹን
ብሎ ያዘዘውን ጉዳይ ያልፈጸመውን ልግደል ልምታ ብሎ መጋበዝ ።
ዱታነኝ ብሎ ለያዥ ለገራዥ አስቸግሮ አረፈደ ።
ዱካ የከብት ጫማ ፊርማ ። ፪/ ፍለጋ ። ዱካው እንኳ ጠፋ ።
ዱዳ በፍጹም የማይናገር ፤ መነጋገር ያቃተው የሚያዳግተው ።
የጉበዝ ዱዳ
ባመቱ ምድረ በዳ ።
፪/ ፈዛዛ ። እዚኽ ግባ የማይባል ዱዳ ነው ።
ዱዳ ቀበሌ ። በዱዳው ሰውም የለ ። ዱዳው ጭር ብሎአል ።
ፉካ እንደ መስኮት የሚወጣ ትንሽ ቀዳዳ ። ፪/ እበት ሽንት የሚወጣበት የበረት
ቀዳዳ ።
ፉጋ የፉንጋ ፉንጋ ። ፉጋ ብጤናት ። ፪/ ገበቴ ሠሪ ፤ በርጩማ ጠራቢ ፤ ራሱ ላይ
እባብ ጠምጣሚ ነገድ ።
ሙሬ ገለባውና ፍሬው ጤፍን የሚመስል ለወፍጮ መጥረጊያ የሚሠራ ሣር ።
፪/ ከዚኹ በቅሎ የተሠራ ፤ የሚሠራ የወፍጮ መጥረጊያ ።
ሙሴ ሙሴ ከውኃ ውስጥ የወጣ ፤ እውኃ ውስጥ የተገኘ ። በትረ-ሙሴ ። አምላከ-ሙሴ
የሙሴ ጽላት ናት የአሮን በትር
ወላዲተ አምላክ የፍቅር መንበር ።
፪/ በማኅበር ውስጥ የሚያስተዳድር ። ሙሴዎች የታሉ?
ቡሄ ጐል ጊዜ በዓመት ባመቱ ነሐሴ ዓሥራ ሦስት ቀን የሚውል የደብረ ታቦር
በዓል ።
ቡሬ ጋልኛ እጀርባው ላይ ነጭ የጣለበት በሬ ። ሻንጉርጉር ።
ዉሼ ሺጂ! ሺድ! (ለአህያ) ። ነጋዴ አህያን ዉሼ! በቅሎን መጭ! እንዳለ ይውላል ፤
ዱቤ እጅ በእጅ ያልተከፈለ ዋጋ ። በዱቤ አይሸጥም ።
ጉሬ ዳቤ ። ከጉሬው ውሰድለት ።
ሉል ሉል ክቡር የኾነ ማዕድን ።
ሉክ እኹለት የታጠፈ ትልቅ ወረቀት ፤ ቅጽ (ለብራና) ።
ሉድ ሉድ የቃየል መንትያ ።
ሙር ዕብድ ። እኹንስ ሙር ኾነ ።
ሙቅ ምውቅ የሞቀ ። ፪/ እንደ አጥሚት ዓይነት ።

አማርኛ ግዕዝ

መ·ትምውት የሞተ
መ·ት መውቀስ ።
ድንጋይ መንከስ ።
መ·ዝ ፍሬው የሚበላ ኮባን መሳይ ተክል ።
መ·ጭ ከዘራን የሚመስል የጤፍ መውቂያ ።
ሩር ጥንግ ። ሩር አጥተን ነው እንጂ ገና እንጫወት ነበር ።
ሩቅ ርኁቅ የራቀ ። በእግር ሩቅ መንገድ መኼድ ያደክማል ።
ከሩቅ ዘመዴ ።
የቅርብ ጐረቤቴ ።
ሩብ ራብዕ ከአራት አንድ ። የኢትዮጵያ ብር ሩብ ኻያ አምስት ሳንቲም ነው ።
ሩት ሩት የሞአባዊት ሴት ስም ። ፪/ መጽሐፈ ሩት ።
ሩዝ የስንዴን ክክ የሚመስል የሚበላ በቀ·ል ።
ሱስ የቡና ጥምና የትንባሆ ጥም ልማድ ። የቡና ሱስ አለበት ።
ሱቅ የመሸቀጫ ቤት ። ወደ ሱቅ ኼደ ።
ሱፍ አገዳው ወርቅማ ፤ የሚበላ ፤ ፍሬውም ነጭ የኾነ ዘር ።
ሹል ዱልዱም ያልኾነ ። ፪/ አፈኛ ። ምን ያለችው ሹል አፍ ናት!
ሹም አለቃ ።
ሹም ቢሞት ቀባሪው ሐምሳ ።
የሹም ልጅ ቢሞት መቶ ሐምሳ ።
ሹሽ በዓይነ ምድር ውስጥ የሚገኙ ጥቃቅን ትሎች ።
ሹጥ ርጥብ ሥጋን በመብላት የሚፈጠር ኮሶን በመጠጣት የሚወገድ የሆድ ውስጥ ትል ።
ቁ̀ቅ ጡጥ (ያመለጠ ፈስ ድምጽ) ። ፈሱን ቁቅ አደረገው ።
ቁብ ጉጕት ወይም ግድ ። ለመጠየስ ቁብም የለኝ ።
ቁ̀ስ ፊጥ ። አናቱ ላይ ቁብ አለበት ።
ቁ̀ጣ የጅራፍ መጨረሻ (ክሮራ ወይም እርሱን ከመሰለ ነገር የሚታከልበት) ።
ቁጭ መቀመጥ ። እባክኽ እወንበሩ ላይ ቁጭ በል ።
ቡሽ እንደ ቄረቆንዳ ያለ በውኃ ላይ የሚንሳፈፍ የጠርሙስ መክደኛ ።
ቡጥ የዳቦ ልብ ። ቅርፊት ቅርፊቱን ጥለሽ ቡጡን ስጪኝ ።
ቡ̀ፍ የውሻ ጩኸት ። ይኸ ውሻ ቡፍም አይል ።
ቡ̀ፍ ተንሰራፍቶ የበቀለ ። ቡፍ ብሎ ወጣ ።

አማርኛ ግዕዝ

ቱስ ጡዝ ፤ ቁቅ ፤ ጢዝ እንቦጭ ያላለ ፈስ ድምጽ ።

ቱሽ አህያን ፤ ቁም እርጋ ፤ ቁሚ እርጊ የሚባልበት ቃል ።

ቱግ ብው (ለቍጣም ይኾናል) ። ያ ነገር መደረጉን በሰማ ጊዜ ቱግ አለ ።

ኑግ መልኩ ጥቍር የኾነ ተልባ መሳይ የቅባት እኽል ።

ኡድ ጣፋጭ ሽታ ያለው የሚጤስ ነገር ።

ኩት ሑት የኮከብ ስም ።

ኩክ እጀሮ ውስጥ የሚገኝ ማር መሳይ መራራ ነገር ።

ኩፍ ማሠረፍ ። እስከ መቼ ኩፍ ብለኽ ትኖራለኽ ። ፪/ ተነፋ (ከመቡካቱ የተ ነሣ) ። ሊጡ ኩፍ ብሎአል ።

ዉሽ አህያን ፤ ኺድ ኺጂ የሚባልበት ቃል ።

ዙር የክበብ ዙሪያ ። ስንት ዙር ሰፋሽ? ዙር ታውቃለችን (በጋገራ) ።

ዱር ዱር ጫካ ። አገሩ ዱር ነው ። ፪/ ውጭ ። እገሌ የት ነው? እዱር ነው ።

ዱግ ከምስለኔ በታች ከጭቃ-ሹም በላይ ያለ ሹመት ፤ ሹም ፤ መጨኔ ። ዱጉን ጥራና አምጣው ። ዱጉም ኢጋፋሪውም እኔ ነኝ ።

ጉም ጊሚ ጥቅጥቅ ያለ ጭጋግ ። ጉም አፍኖ ዋለ አይደለም እንዴ?

ጉብ ፊጥ ። እሰውየው ላይ ውሻው ጉብ አለበት ። ምን ጉብ ቂጥ ያደርግሻል= ምንቁጭ ብድግ ያደርግሻል ።

ጉብ ከፍ ባለ ቦታ ላይ ተንዘራፍጦ ጉች ማለት ። አልጋው ላይ ጉብ ብሎአል ።

ጉች ጉቶ መስለሎ ቁብ ማለት ። ምነው ብቻኽን ጉች ብለኻል ።

ጉድ እጹብ ። ጉድ የኾነ ቤት አሠራ ። ጉድ ነሽ የአንኮር ቅጠል ከመለምለ ምሽ የመለብለብሽ ። ፪/ ጀሮ ያልሰማው ዓይን ያላየው አዲስ ፍጥረት (ነገር) ። ጉድ ወለደች ። ፫/ ተሠውሮ የነበረ ነውር ። ጉዴ ወጣብኝ ። ጉድ ፈላብኝ ።

ጡል ቢስ የሌለው። ልበ ጡል ። ቀልበ ጡል ።

ጡር ጭቦ ፤ ግፍ ። ጡርን መፍራት ይጠቅማል ። የእኽል ጡር አለው ። ጡር ነው።

ጡር ያረ የተሸከመ ፤ የተሸከሙት ። ነፍሰ-ጡር ናት=እርጉዝ ናት ።

ጡብ ለግንብ የሚኾን የተተኰሰ ሸክላ ። ጡብ ይሠራል ።

ጡብ ዱብ ። በመስኮት ጡብ አለና ኼደ ።

ጡት ጥብ (ለሰው ሲኾን) ። አንድ ጋት ያኽል ከእልቅት በታች ርቀት ያለው ወተት የሚወጣው ፤ ሕፃናትም የሚጠቡት ፤ በሴት ላይ ጐልቶ የሚታይ ክፍለ አካል ።

አማርኛ ግዕዝ

ጡን ጡዝ ። ይኽ ሕፃን ጡን ጡን እንዳለ ዋለ ።

ጡዝ ሎፍ ። እንዲኹ ከአንዱ ወደ አንዱ ጡዝ ጡዝ እንዳለ ዕድሜውን አሳለፈው አይደለምን?

ጡዝ በድንገት የተፈሳ ፈስ ድምጽ ።

ጨል ጭልፊትን የመጥሪያ ቃል ።

ፉር ፈረስ ወይም በቅሎ ፤ በጠቅላላ የጋማ ከብት የአውሬ ጠረን ሲሸተው በአፍንጫው የሚያሰማው ድምጽ ።

ፉር እጣ ። ፉር ወጣበት ።

ፉት ጉንጭት ፤ ጭልጥ ። ትምህርቱን ፉት አላት ። ከቀረበለት ጠላ ጥቂትም ፉት አላለለት ።

ሙሎ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ክፍለ አገር ።

ሙሾ አምቀሽ የልቅሶ እንጉርጉሮ ። ሙሾውን ስታሳምረው አረፈደች ።

ቡሎ ሸክላ (ለፈረስ) ። ባለ ቡሎ ፈረስ ነው ።

ቡሎ የልብስን መልክ ለማጠየም የሚያገለግል ቀለም ። ቡሎ ንከረው ።

ቡኮ ብጉዕ የቦካ ሊጥ ። ቡኮውን ውሻ ደፋው ።

ኑሮ አነዋነዋር ። አገሩ ለኑሮ አይስማማም ። ኑሮኽ እንደምንድን ነው?

ኩሎ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ክፍለ አገር ።

ዉሎ ልቅሶ ። እገሊት እዉሎው ውላለች?

ዱሮ ጥንት ፤ ቀድሞ ። ዱሮ በእኛ ዘመን እንዲኽ ነበር ።

ጉሎ ቅጠለ ሰፋፊ ፤ አገዳው ቀይ ፤ ፍሬው ኻንጉርጉር የኾነ ተክል ። ጉሎ ዘይትን ጠጥቶአል ።

ጉቦ ለፍርድ ማጣመሚያ የሚሰጥ ገንዘብ ። ጉቦ በላ ። በጉቦ ገዛው ።

ጉቶ የዛፍ ቂጥ ። ዛፍ ሲጣል ከሥሩ ጋራ የሚቀረው ክፍል ።

ጉቾ አነስተኛ ክምር ። ብዙ ጉቾች አየኹ ።

ጡሰ ሰብአዊ ሥራ የኾነ ጡት ። ጡጦውን ስጪው ። ጡጦውን ይጥባ ።

ፉሎ ጋልኛ ልባብ ። ከፊት በኩል የሚውል ። የበቅሎው ፉሎ የት አለ? ፪/ መረን መለቀቅ ። ፉሎው ሲወልቅለት ጊዜ ማን ይቻለው!

ፉሮ ጋልኛ ፉር የሚያሰኝ የጋማ ከብት በሽታ ፤ የጋማ ከብት ጉንፋን (ንፍጥን የሚያስመጣ) ።

አማርኛ ግዕዝ

ሊሙ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ክፍለ አገር ።

ሊባ ሊባ ከደቡብና ከምዕራብ መኽል የሚገኝ ማዕዝነ ዓለም ።

ሚና ፊና ፤ ጐራ ፤ ወገን ። በሚናኽ ተጫወት ።

ሪና ቀኝ ። ጌታችን መድኃኒታችን በአባቱ ሪና ተቀመጠ ።

ሲላ ዶሮ የምትለቅም መጠነኛ አሞራ ።
ዕብድ አሞራ
ሲላ ደንገጡራ ።

ሲቃ የጀግና እልክ ። ፪/ ከእሩጫ ከድንጋጤ የተነሣ ለመናገር የሚያውክ የእስትንፋስ እጦት ።

ሲና ሲና በዓረብ ሀገር ያለች ተራራ ።

ቂጣ ጥፍጥፍ ፤ ሙልሙል ፤ ትንሽ ዳቦ ።

ቢያ ወይ ። ኧረ እንዲኽ አይደለም ። የወዳጅ ትግያ
ብትወድቅን ትሰበር ብለኽኝ ነው ቢያ ።

አያ የመጽሐፈ አያሱ ወልደ ነዌ ከፊለ ስም ።

ዒጣ በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ የሚገኝ አውራጃ ።

ዲዳ ግልጽ ያልኾነ ንግግር የሚናገር ። ዲዳን ማን አፈ-ጉባኤ ያደርጋል?

ዲና ዐመፀኛ ፤ ሸፍታ ፤ ያልገበረ (አገር ፤ ሕዝብ) ። ዲና ገባ ። ፪/ወረረ ፤ ድል አደረገ ። ዲና መታ ። አባ/ዲና=ዐመፀኛን ለጥ ሰጥ አድርጎ የሚገዛ ።

ጊዳ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ክፍለ አገር ።

ፊላ ረዥም ከሰው ቁመት በላይ የኾነ ጥቅጥቅ ያለ በመልክ መቃን የሚመስል ለገሳ የሚኾን ቅጠል ።

ፊና ሚና ፤ ጐራ ፤ ወገን ። በፊናኽ ተጫወት ።

ፊኛ የሽንት ማጠራቀሚያ የኾነ የአካል ክፍል ። ፊኛው አይቋጥርለትም ።

ፊጋ ጋልኛ ርዋጭ ፤ ደንብሮ የሮጠ ። ፊጋ በሬ ።

ሚዜ የምታገባውን ልጃገረድ ከእኅቱ አልለያትም ብሎ ለሙሽራው ከእናት ከአባትዋ የሚቀበልለት ።
የሚዜ ፈዛዛ
የለውም ለዛ ።

ሺራ በትግሬ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ የሚገኝ አውራጃ ።

ጊቤ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ወንዝ ።